

የይሁዳ
መልእክት
አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ
ሃይማኖት መጋደል
ዘላለም መንግሥቱ

የይሁዳ መልእክት

አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት መጋደል

ከዘላለም መንግሥቱ

የይሁዳ መልእክት

አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት መጋደል

ዘላለም መንግሥቱ (© ፪ሺህ፲፭ ዓመተ ምሕረት)

ይህን መጽሐፍ ባለቤትነቱን ሳይወስዱና ለሽያጭ ሳያውሉ ጸሐፊውን በማሳወቅ ማባዛትም ማሰራጨትም ይፈቀዳል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት በ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ካሳተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ሽፋን፤ ዘመን ግራፊክስ

* * * * * *

The Epistle of Judas


Contending for the faith once delivered.

Zelalem Mengistu (© 2022)

This work can be reproduced and disseminated by only notifying the author, without claiming ownership, and so long as it is not for profit.

All Scripture quotations are from the 1962 edition of the Amharic Bible published by the Bible Society of Ethiopia.

Cover Design: ZeMen Graphics



ማውጫ

ማን ጻፈው? ለማን ጻፈው? ለምን ጻፈው? ቁ. 1-3

የጻፈበት ዋና አሳብ፤ የተጋድሎው ምክንያቶች፤ ቁ. 4

ማስጠንቀቂያው፤ 5-16

የከሐድያን ፍርድ ከታሪክ፤ 5-7

የወደቁ እስራኤል፤ ቁ. 5

የወደቁ መላእክት፤ ቁ. 6

ሰዶምና ገሞራ፤ ቁ. 7

የከሐድያን መልክ ከዘመኑ፤ 8-16

ተሳዳቢነት፤ ቁ. 8-10

የቃየን መንገድ፤ ቁ. 11

የበለዓም ደመወዝ፤ ቁ. 11

የቆሬ መቃወም፤ ቁ. 11

ባሕርያቸው፤ እድፈኞች፥ ነውረኞች፥ የራሳቸው እረኞች፥ ደረቅ ደመናዎች፥ የተነቀሉ ዛፎች፥ የሚንከራተቱ ከዋክብት፤ ቁ. 12-13

የፍርዳቸው ትንቢት፤ የሄኖክ ትንቢት፤ ቁ. 14-16

ምክር ለአማኞች፤ 17-23

ወዳጆችና ዘባኞች፤ ቁ. 17፥19

ወዳጆች ሆይ . . .፤ ቁ. 20-23

ቡራኬ፤ ቁ. 24-25

መግቢያ

ይህ ዘመን ከመቼውም ይልቅ ሐሰተኛ ነቢያት የበዙበት ነው። ሐሰተኛ ነቢያትና የሐሰት አስተማሪዎች የሐሰት አባት ሰይጣን በዔድን ገነት ሔዋንን ካሳተባት ጊዜ ጀምሮ ነበሩ። እስከ ፍጻሜ ዘመናትም ይቀጥላሉ። በብሉይ ኪዳንም ነበሩ፤ በጌታ ዘመንም ነበሩ፤ በሐዋርያቱም ዘመን ነበሩ። ዛሬም በእኛ ዘመን በዝተው ይገኛሉ።

ይሁዳ መልእክቱን በጻፈበት ዘመን ሐሰተኞች አሳሳቢ ሆነው ነበር። ይህ ችግር ይሁዳን የመልእክቱን ይዘት እስከማስቀየር ያደረሰው አሳሳቢነት ጉዳይ ነበረ። ስለዚህ ነው በቁጥር 3 ላይ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። ያለው።

ዛሬም የሐሰተኛ ነቢያት ጉዳይና ብዛት አሳሳቢ ነው። ቅዱስ ቃሉ የሚያስተምረንም በመጨረሻው ዘመን ይህ አሳሳቢነት እንደሚቀንስ ሳይሆን እንደሚጨምር ነው። ጌታ ይህን አስተምሮአል። በማቴ. 7፥22 በዚያ ቀን <u>ብዙዎች</u>፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ ኃጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። ብሎአለ። በማቴ. 24፥5 እና 11 <u>ብዙዎች</u>፦ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ብሎአል። ሐዋርያው ዮሐንስም ከማሳሰቢያ ጋር፥ ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው፥ የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ <u>ብዙዎች</u> የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደ ሆነ እናውቃለን። ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ <u>ብዙዎች</u> ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። ብሎአል፤ 1ዮሐ. 2፥18 እና 4፥1።

ይሁዳ ይህን አሳሳቢ ጉዳይ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ሲጽፍ ይህን አስተውሎአል። በጣም በግልጽ ቋንቋና በብዙ ምስላዊ ምሳሌዎችም ኡድምቆ ነው የጻፈው። ማስጠንቀቁ በእጅጉ አስፈላጊ ነበር። በዚህች አጭር ለግል ንባብም ለቡድን ጥናትም የተዘጋጀች ሐቲት ይህንን የይሁዳን አሳሳቢና አስጠንቃቂ አሳብ እንካፈል።

ዘላለም መንግሥቱ

1፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ፥ በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ፤

2፥ ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ።

3፥ ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።

4፥ ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሦቻንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ።

5፥ ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብፅ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

6፥ መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።

7፥ እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።

8፥ እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉ።

9፥ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር፦ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም።

10፥ እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥ አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ።

11፥ ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል።

12፥ እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ እንደ እድፍ ናቸው፤ እንደ እረኞች ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይጠብቃሉ፤ በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው ደመናዎች፥ ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ ከነሥራቸው የተነቀሉ በበጋ የደረቁ ዛፎች፥

13፥ የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል፥ ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው።

14-15፥ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ፦ እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭካና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።

16፥ እነዚህ እንደ ምኞታቸው እየሄዱ የሚያንጎራጉሩና ስለ ዕድላቸው የሚያጕረመርሙ ናቸው፥ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ አፋቸው ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል።

17፥እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ፤

18፥ እነርሱ፦ በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባኞች ይሆናሉ ብለዋችኋልና።

19፥ እነዚህ የሚያለያዩ ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

20፥ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥

21፥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።

22፥ አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፥ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥

23፥ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።

24፥ ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው፥

25፥ ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን።

ማን ጻፈው?

ማን ጻፈው? በግልጽ እንደተጻፈው የይሁዳን መልእክት የጻፈው ይሁዳ ነው። ‘የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ፥’ ይላል። ይህ ይሁዳ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ መሆኑን ነው የጻፈው። በዘመኑ የእገሌ ልጅ እገሌ እንጂ የእገሌ ወንድም እገሌ ብሎ መልእክት መጻፍ የተለመደ አይደለም።

ያዕቆብ ራሱ ማን መሆኑን መመልከት ተገቢ ነው። ይህ ያዕቆብ የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ አይደለም። የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ቤተ ክርስቲያን ገና ጨቅላ ሳለች ሔሮድስ በሰይፍ አስገድሎታል፤ ሐዋ. 12፥1-2። ይህ ያዕቆብ የያዕቆብን መልእክት የጻፈው በኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን የታወቀው መሪ ነው። ይህ ያዕቆብ ከጌታ ወንድሞች አንዱ ነው። ከትንሣኤው በኋላ በጌታ ያመነና በመልእክቱ ውስጥ ራሱን የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ብሎ የጠራ ሰው ነው ያዕ. 1፥1።

በገላ. 1፥18-19 ሐዋርያው ጳውሎስ በዓመታት በኋላ ከደማስቆ ወደ ኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ስላገኛቸው ሰዎች ሲናገር፥ “ከዚህ ወዲያ ከሦስት ዓመት በኋላ ኬፋን ልጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቼ ከእርሱ ጋር አሥራ አምስት ቀን ሰነበትሁ፤ ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ከሐዋርያት ሌላ አላየሁም።” አለ። ከሐዋ. 15፥13 ጀምሮ እንደምናየው ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ሽማግሌ ነው።

የጌታ ወንድሞች እየተባሉ በስም ስለተጠቀሱት፥ ማቴ. 13፥55 እንዲህ ይላል። “ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን?” ያዕቆብ ከጌታ ወንድሞች አንዱ ነው። በማር. 6፥3ም ይኸው ተጽፎአል። ስለ ወንድሞቹ በተጨማሪ ማቴ. 12፥46-55፤ ማር. 3፥31-34፤ ሉቃ. 8፥19-21፤ ዮሐ. 2፥12፤ 7፥3-10፤ ሐዋ. 1፥14፤ 1ቆሮ. 9፥5፤ መመልከት ይረዳል። እነዚህ ወንድሞች ከጌታ በኋላ ከማርያም የተወለዱ የዮሴፍ ልጆች እና የጌታ ግማሽ ወንድሞች ናቸው። ይህ ይሁዳ የያዕቆብ ወንድም ነው፤ የጌታም ወንድም ነው። ሆኖም፥ ያዕቆብም፥ ይሁዳ ራሱም ራሳቸውን የጌታ ወንድም ሳይሆን የጌታ ባሪያ ብለው ነው የጻፉት። በእርግጥም የጌታ ባሪያም ናቸው፤ ጌታ በእውነት ጌታ ነውና። ከላይ ባሉት ጥቅሶች ውስጥ እንደምናየው ግን ራሳቸው ራሳቸውን እንደዚያ ባይጠሩም፥ ሌሎች በስም ጠቅሰው የጌታ ወንድሞች መሆናቸውን ጽፈዋል።

ያዕቆብና ይሁዳ ራሳቸውን እንደ ጌታ ባሪያ እንጂ እንደ ጌታ ወንድሞች ያለመጥቀሳቸው ያላቸው ተሰሚነትና ተደማጭነት ካልላቸው ቀረቤታና ግንኙነት

የተነሣ እንዳይሆን በማሰብ ነው ተብሎ ይገመታል። እንግዲህ ይህ ይሁዳ የጌታ ግማሽ ወንድም መሆኑን ልብ እንበል።

ግማሽ ወንድም ሲባል ግር ይላል። የጌታ ወንድም ሲባል የእግዚአብሔር ወንድም እያሉ የሚያፈዙ ቢኖሩ አያስገርምም። ጌታ ሰዋምላክ፥ ፍጹም ሰው እና ሙሉ አምላክ መሆኑን ካመንን ያዕቆብ ወይም ይሁዳ የአምላክ ወንድሞች ማለት የምንለውን ያህል የሰው ወንድሞች መሆናቸውን መቀበል ሊሳነን የተገባ አይደለም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ ትምህርት የምናገኘው እውነት ማርያም ዘላለማዊ ድንግል አለመሆኗን፤ ኢየሱስን በድንግልና ከወለደች በኋላ ሌሎች ልጆችን መውለዷን ነው። ይህ፥ 'አበስኩ ገበርኩ' አያሰኝም። ትልቁ ጥያቄ፥ 'ማመን ያለብን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ነው? ወይስ የሰዎችን ፈጠራ?' የሚል መሆን አለበት።

ስለ ዮሴፍ የተነገረውም፥ የበኩር ልጅዋንም እስከትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው። ተብሎ ነው፤ ማቴ. 1፥25። እስከ. . . ማለት እስከ ማለት ነው። እስከ የሚያበቃበት እና ከእስከ የሚቀጥል ሌላ መኖሩ መደበኛው የ 'እስከ' አካሄድ ነው። የማርያም ዘላለማዊ ድንግልና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቶም የማይገኝ ሰው ወለድ ትምህርት ነው። ስለዚህ የጌታ ወንድሞች እየተባሉ በስም የተጠቀሱ መኖራቸው እና እኅቶቹም መጠቀሳቸው የሚያሳየው ማርያም ከዚያ በኋላ መውለዷን ነው። ይህ ግልጽ ነው። የማርያም ከዚያ በኋላ መውለድ የጌታን ጌትነት ከቶም ዝቅ አያደርገውም። የማርያምንም ብጽዕና ቅንጣት ታህል አይቀንሰውም።

ባደግንበት እንደ መርግ ተጭኖን በኖርነው ኦርቶዶክሳዊ ባህል ማርያም ዘላለማዊ ድንግል መሆንዋ፥ ዮሴፍ አረጋዊ ጠባቂዋ መሆኑ፥ የጌታ ወንድሞች የተባሉት ዮሴፍ ከሞቶች የቀድሞ ሚስቱ የተወለዱለት ልጆቹ መሆናቸው እየተነገረን ነው ያደግነው። ይህ በእጅጉ ተጋንኖ የተጻፈው በተአምረ ማርያም ነው። ስለ ተአምረ ማርያም በ2012 በሰፊው የጻፍኩትን hhttp://books.good-amharic-books.com/enoch.pdf ማግኘት ይቻላል። ይህ ያኔ በተከታታይ ከጻፍኩበት ሦስት ክፍሎች ሦስተኛው ነው። ብዙዎቻችን መጽሐፉን አናውቀውም። ግን ብዙ ቅሌቶች የሞሉበትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ፈጽሞ የሚጋጭ፥ ድነትን የምናገኝበትን የክርስቶስን የተፈጸመ መሥዋዕትነት የሚያራክስ የፈጠራ ሥራ ነው።

ሌላው መርሳት የሌለብን ኢየሱስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ሳይሆን አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ነው። ያ ባሕርይ አንድ የተዋሕዶ ባሕርይ (ሞኖፉሲስ) ነው። ስለዚህ ነው ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ሞኖፊሳይት (የአንድ ባሕርይ አማኞች) የሚባሉት። ያ የተዋሓደ ባህርይ ስብዕናውን የዋጠ መለኮታዊ ባሕርይ ነው። ስለዚህ ነው የጌታ ወንድሞች

ሲባል የእግዚአብሔር ወንድሞች የሚሉ የኖሩት። ምክንያቱም የተማሩት የኢየሱስ ሰብዓዊ ባህርይ በመለኮታዊው ባሕርይ ውስጥ መሟሟቱን ነው።

ለማን ጻፈው?

1፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም የሆነ ይሁዳ፥ በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ፤ 2፥ ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ።

ይህኛው፥ 'ለማን ጻፈው?' የሚለው ጥያቄ፥ 'ማን ጻፈው?' እንደሚለው አወዛጋቢ አይደለም። ለነገሩ፥ ያኛውም (ማን ጻፈው የሚለው) አወዛጋቢ መሆን አልነበረበትም። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የቀደመ እውቀታችንን መሞገት ሲኖርበት የቀደመ እውቀታችን እና ትውፊታችን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እንዳንቀበል ሲያስገድደን ችግር ነው።

ለማን ጻፈው? ‘በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ፤’ በአብ የተወደዱ፥ ለኢየሱስ የተጠበቁ፥ የተጠሩ። የይሁዳ መልእክት ለአንድ አጥቢያ የተጻፈ ሳይሆን የተወደዱ፥ የተጠበቁ፥ የተጠሩ የሚሉት ቃላት በጥቅል ለአማኞች የተጻፈ መሆኑን ያሳያል። በዚህ ምክንያት ከጠቅላላ መልእክቶች ተርታ የሚመደብ ነው። በቁ. 3፥ 17 እና 20 ‘ወዳጆች’ ስለሚልም ጠቅላላ መልእክት ነው። መልእክቱ እንዲህ ሰፊ ከሆነ ይሁዳ የጻፈበት ጉዳይም ያን ያህል በስፋት የናኘ ጉዳይ ነበር ማለት ነው። ይህ መልእክት በቀጥታ ለእኛ የተጻፈ ባይሆንም፥ ቃሉ ሕያው፥ ዘመንና ድንበር ተሻጋሪም ነውና የዛሬና የእኛም ነው።

ስለ ጉዳዩ በሌሎች ጥቅሶች ውስጥ ይሁዳ በስፋት አውስቶታል። በዚህ ጥቅስ ግን የተጻፈላቸው ሰዎች የተገለጡበትን መልክ ስናይ በአብ የተወደዱ ናቸው። መልእክቱ የዛሬና የእኛም ነውና እኛም በአብ የተወደድን ነን። ዮሐ. 3፥16 ይህንን የአብን ፍቅር በግሩም ይገልጠዋል። “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ” 1ዮሐ. 3፥1 ደግሞ እንዲህ ይላል፤ “የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።” እንዲህ ያሉ በመቶ የሚቆጠሩ ጥቅሶችን ማየት ይቻላል። የአብ ፍቅር ድንቅ ነው።

እነዚህ ሰዎች የተወደዱ ብቻ ሳይሆኑ ተጠብቀው የተጠሩም ናቸው። መጠበቅ የሚለው ተመሳሳይ ቃል በቁ. 6 እና 13 ተጠቅሶአል። ያ የዚህኛው ተቃራኒ ነው። ያ ለፍርድ እና ቅጣት መጥጠበቅ ነው። ይህ ግን ለክርስቶስ መጥጠበቅ ነው።ድነታችንን ስናስብ ይህ እውነት እጅግ ሊያስደስተን የተገባው ነው። ይህ ከዳንን በኋላ የምንጠበቀው ጥበቃ ሳይሆን በፊትም ጀምሮ ያለ ከመጠራታችን ጋር የተያያዘ ጥበቃ ነው። ከዳንን በኋላ ሳንሰናከል እንደሚጠብቀን ይሁዳ በቡራኬው ቃ ጽፎታል፤ ቁ. 24።

ሌላው ትልቅ ቃል መጠራት የሚለው ነው። ክርስቲያኖች የተጠራንና ለጥሪ መልስ የሰጠን ሰዎች መሆናችንን መረዳት አለብን። መዳናችንን እንድንደነቅበት የሚያደርገን ነገር ጥሪና ጠሪ መኖሩ ነው። ጥቂት ጥቅሶች፥ ለምሳሌ፥ ሮሜ 1፥6-7፤ 1ቆሮ. 1፥2 እና 24 ይህንን መጠራት ይናገራሉ።

ከተቀባዮቹ ቀጥሎ ሰላምታውን ያቀርባል። ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ። ምሕረት፥ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው የእርሱ ርኅራኄ ነው። በክርስቶስ በኩል የተቀዳጀነው የበደላችን ስርየት ነው። ሰላም በምንም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በእርሱ ውስጥ የሚገኝ ዕረፍትና እፎይታ ነው። ፍቅር ኃጢአተኞቹ እኛ የተወደድንበት መወደድ ነው። ይሁዳ የተመኘው የጻፈላቸው ሰዎች እነዚህ ነገሮች እነዚህ እንዲኖሯቸው ሳይሆን እንዲበዙላቸው ነው የተመኘው። ይህ ማለት ቀድሞውኑ አሏቸው ማለት ነው። ይሁዳ የጻፈላቸው እነዚያ እና የጻፈልን እኛ እኒህ ነን።

ለምን ጻፈው?

3፥ ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆኑብኝ።

ማን እንደጻፈው እና ለማን እንደተጻፈ አየን። ለምን እንደተጻፈ ደግሞ እንይ። ከዚያ በፊት ግን በይሁዳ መልእክት ቀኖናዊነት (ከቅዱሳት መጻሕፍት ተራ መቆጠር) ጥቂት እንይ።

በቅዱሳት መጻሕፍት የቀኖና ታሪክ ውስጥ ይሁዳ እንዳይቆጠር ያሰቡ አበውት ነበሩ። ጥቂቶቹ ይህን ያሰቡት በቁጥር 9 እና 14 ከቀኖና ውጪ ያሉ ምንጮችን በመጥቀሱ ምክንያት ነው። በጤናማ ዳኝነት ሲታይ ግን የተጠቀሱት ምንጮች እስትንፋሰ መለኮት የሌለባቸው መጻሕፍት ሆነው ለታሪካዊነታቸው፥ ለምሳሌነታቸውና ለይዘታቸው ሊጠቀሱ ይችላሉ። በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፏቸው ሰዎች ጠቀሷቸው ማለት ግን እነዚያ ተጠቃሾች ተቀባይነት የተቀዳጁ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው ማለት አይደለም።

ጳውሎስ በአቴና በአርዮስፋጎስ ሳለ ሲናገር የራሳቸውን ባለ ቅኔ ጠቅሶ ተናግሮአል፤ ሐዋ. 17፥28። ለቲቶ ሲጽፍ ደግሞ በቲቶ 1፥12 የቀርጤስ ሰዎች ነቢይ የሆነ ሰውን ጠቅሶአል። ይህ ሰው በታሪክ ሊቃውንት ዘንድ ኤፒማኒደስ ተብሎ የሚታወቀው ሰው ነው። የአቴናው ባለ ቅኔ ወይም የቀርጤሱ ነቢይ በጳውሎስ መጠቀሳቸው ቀኖናዊ እንደማያደርጋቸው ሁሉ ይሁዳም የአጵቅሪፋ መጻሕፍትን መጥቀሱ መጠቀሳቸውን እንጂ ቀኖናዊ መሆናቸውን አያሳይም።

የይሁዳ መልእክት መቼ ስለመጽፃፉም እርግጠኛ ውስጣዊ ማስረጃ አናገኝም። ቀደም ሲል ካየነው የይሁዳ ዕድሜ መገመት እንችላለን። በቁ. 17-18 ላይ ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ተቀባዮች የሐዋርያትን ትምህርት የሰሙ ያስመሰላቸዋልና ከሐዋርያት የሰማ የመጀመሪያ ትውልድ ዘመን ነው ያሰኛል። ሌላው ይሁዳ የሚጠቅሳቸው የስሕተት ትምህርቶች ኋለኛ የስሕተት ትምህርቶች ሳይሆኑ የመጀመሪያ ዘመን ስሕተቶችና ችግሮች ናቸው። ጳውሎስ በሐዋ. 20፥29-30 ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ። ብሎ ነበር። ይሁዳ ስለእነዚህ ጨካኞች ጽፎአል። በሮሜ 6፥1 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ያለው በይሁዳ መልእክት በተግባር የታየ ነው። በ1ቆሮ. 5፤ 2ቆሮ. 12፥21፤ ኤፌ. 5፤ 1ተሰ. 4 የሚታዩት ዝሙት፥ አርነትን ለሥጋዊነት መጠቀም፤ ርኩሰትና ዓለማዊነት፥ መኖር ችግሩከአስተምህሮታዊ ዝንፈት የበለጠ የርኩሰትና የሥጋዊነት ችግር መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ ከሐዋርያት ዘመን ተከትሎ በነበረው ዘመን ውስጥ የተጻፈ ነው።

ለምን ተጻፈ? ይሁዳ በግልጽ እንደጻፈው ሊጽፍ የጀመረው “ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ . . .” እንዳለው ስለ ድነት ነው። ምናልባት ልክ ጳውሎስ በሮሜ ውስጥ እንደጻፈው ያለ ወይም ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን የሚመስል ሰፊና ጠንካራ የድነት ስነ መለኮት ሊጽፍ ተነሣስቶ የነበር ይመስላል። ነገር ግን ስለዚህ ‘ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን’ ስላለው ጉዳይ ሊጽፍ ፈልጎ በመልእክቱ ውስጥ ስለምናየው የስሕተት ትምህርትንና ልምምዶችን ስለመጋፈጥ ሲጽፍ ይታያል።

ለምን? ለምን ስለ መዳናችን አልጻፈም? ለምን ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንዲጋደሉ እየመከረ ይጽፍ ዘንድ ግድ ሆነበት? ይህን ያደረገው የስሕተት አስተማሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሾልከው ገብተው የእግዚአብሔርን ጸጋ በሴሰኝነት በመለወጥ አማኞችን ከእግዚአብሔር መንገድ ፈቀቅ በማድረጋቸው ምክንያት ነው። እንዴት እና በምን በምን መሰርይ መንገድ ከመንገዱ ፈቀቅ እንዳደረጓቸው በቀጣዮቹ ብዙ ጥቅሶች ውስጥ ጽፎአል።

ለምን እንደጻፈ ዋናውን፥ መንደርደሪያውን ምክንያት የምናገኘው ሲጽፍ የመከራቸውን ዐቢይ ጉዳይ ምንነት ስናጤን ነው። “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።” ነው ያለው። ለቅዱሳን የተሰጠው ሃይማኖት ወይም እምነት አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠ ነው። ለአንዴና ለመጨረሻ የተሰጠ፥ ተደጋግሞ የማይሰጥ፥ ተደጋግሞ የማይቀበሉት እምነት ነው። የማይሻሻል፥ እያረጀ የማይታደስ፥ አዳዲስ ነገሮችና ቅጥያዎች በላዩ የማይቀጠሉበት ሃይማኖት ነው። ይህ ክርስቶስን ማመን ሐዋርያት የሰበኩት የክርስቶስ መስቀል ነው። ከመዳን በኋላ መዳንን ሙሉ የሚያደርግ ምንም የሚጨመር ነገር የለም።

መጋደል ያስፈለገው ይህንን መስቀል የሚደብቁ፥ የሚሰውሩ፥ የሚለውጡ፥ የሚሸቅጡ ሐሳውያን አስተማሪዎችና ሐሰተኛ ነቢያት ገና ከመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያንን ማዋከብና ማናወጥ፥ መሸርሸርና ማፍረስ ጀምረው ስለነበረ ነው። መጋደል ጠንካራ ቃል ነው፤ መታገል፥ መዋጋት፥ መፋለም ነው። ይህ መጋደል የሥጋና ደም መጋደል አይደለም። የመልእክቱ ዋና አሳብም ሐሰተኛ አስተማሪዎችና ነቢያት ሾልከው ገብተው የፈጠሩት ጉዳት ነው። ጉዳቱ አካላዊ ሊሆን ቢችልም ይልቁን መንፈሳዊ ነው። ይህ ዝም የማይባል ክፉ ጉዳት ነው። ይሁዳ ሊጽፍ የተገደደው በዚህ ምክንያት ነው።

ይሁዳ ሊጽፍ የተገደደበት ጉዳይ እኛንም ይመለከታል። ይህ ያለንበት ዘመን ከይሁዳ ዘመን ካልከፋ አይተናነስም። ሐሰተኛ ነቢያትና የስሕተት አስተማሪዎች በየቀኑ በደርዘን የሚቀፈቀፉበት ዘመን ነው። ስለዚህ ይህ መልእክት እኛንም ይመለከታል። በሥጋና ደም ኃይል ሳይሆን መጋፈጥ፥ መታገል፥ መፋለም፥ መጋደል ለእኛም ነው። መንፈሳዊ ውንድነና ፋኖ የተሰማራበት ዘመን ነውና።

የተጋድሎው ምክንያቶች እነማን ናቸው?

4፥ ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ።

ይሁዳ እየጻፈ ያለው ስለ ሐሰተኞች ነው። እነዚህ ሐሰተኞች በብዙ ቃላትና መግለጫዎች ተገልጠዋል። ይሁዳ ከስማቸው ይልቅ ግብራቸውና መልካቸው ላይ ያተኮረ ማስጠንቀቂያ ነው የጻፈው።

1. ከቀድሞም ለፍርድ የተጻፉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የዳኑ አለመሆናቸውን የሚገልጥ ቃል ነው። እነዚህ ሰዎች ሲጀመርም ከድነት ጋር ግንኙነት የሌላቸው፥ ከጌታ ጋር ትውውቅ የሌላቸው፥ ዓላማና ግባቸው በራሳቸው ለራሳቸው የተቀረጸ የሰይጣን መሳሪያዎች ናቸው።

2. ሾልከው ገብተዋል። እንዳይገቡ እያስጠነቀቀ፥ የቀዳዳ መድፈን ዘመቻ እያስተባበረ አይደለም። እነዚህ ሰዎች ቀድሞውኑ ገብተዋል። ውስጥ ናቸው። ኬላው ተሰብሮ፥ በሩ ተበርግዶ አይደለም የገቡት። ቢሆን ይታወቁ ነበር። ግን ሾልከው ነው የገቡት። አደገኝነታቸውም ይህ ነው።

ይህ ሾልኮ መግባት የሚለው ቃል παρεισδύνω (ፓሬይስዱኖ) ተደብቆ መጥቶ ከጎን መቀመጥ፥ መስፈር፥ መደላደል ማለት ነው። ብዙውን ጊዜ ሐሰተኞች ከውጪ እያንኳኩና በር እየሰበሩ፥ እየበረገዱና እየተንደረደሩ አይገቡም። ከውስጥ ነው ብዙዎች ሐሰተኞች የሚወጡት። ሲወጡ በግልጽ ይውጡ እንጂ ሲገቡ በስውር ሾልከው ነው የሚገቡት። ይህ የማናቸውም የስሕተት ትምህርትና አሠራር ነው። ተደባልቀው ሲኖሩ ሐሰተኛ ነቢያት መሆናቸው የሚያሳውቅ መለዮና መታወቂያ የላቸውም። ከማንም የቤተ ክርስቲያን ሰው አንዱን መስለው ሊታለፉ ይችላሉ። የሚታወቁት ጥፋትና ጉዳት ከሆነ በኋላ እጅግ ዘግይቶና ቆይቶ ነው።

3. ኃጢአተኞች ናቸው። ቃሉ መንፈሳዊነት፥ አማኝነት፥ እግዚአብሔርን መምሰል ከቶም የሊላቸው ማለት ነው። ቃሉ ኃጢአትን ማድረግን ሳይሆን ጨርሶውኑ እግዚአብሔርን አለመፈለግን፥ አለመከተልን የሚያሳይ ነው።

ኃጢአት በተግባር የሚታይ ምንነት ቢኖረውም ዋናው መነሻው ከሚደረገው ነገር በፊያ ያለው የልብ ዝንባሌ ነው። ኃጢአት ቅርንጫፉ ቢሆን ይህ ግንዱ ነው። የዚያ

ሰው ልብ እግዚአብሔርን የሚፈልግና የሚከተል ነው ወይስ ከእግዚአብሔር በተቃራኒው መንገድ የሚሄድ ነው?

4. ጸጋውን በሴሰኝነት ይለውጣሉ። ጸጋው ነጻ ድነትን ያገኘንበት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ጸጋ ነጻ ነው፤ ግን ርካሽ አይደለም። ደኅንነት ነጻ ነው ግን ነፍስ የተከፈለበት ነው። ያውም የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ሞት የተጠየቀበት ነው።

ይህ ጸጋን በሴሰኝነት መለወጥ ለሥጋ የኃጢአትን ፈቃድ መስጠት ነው። ሴሰኝነት የሚለው ቃል በኤፌ. 4፥19፤ 2ጴጥ. 2፥7፥18፤ እና እዚህ ሴሰኝነት ሲሰኝ በሌሎች ጥቅሶች ውስጥ (ማር. 7፥22፤ ሮሜ 13፥13፤ 2ቆሮ. 12፥21፤ ገላ. 5፥19፤ 1ጴጥ. 4፥3) መዳራት ተብሎአል። ለሥጋ ምኞት፥ በተለይም ለብልግናና ለዝሙት አልፎ መሰጠትን የሚያመለክት ቃል ነው። ይህ ጸጋን በሴሰኝነት መለወጥ ይቅርታና ንስሐ በቀላሉ እንደሚገኝ፥ በጸጋና በይቅርታ እያሳበቡ ሥጋንም እያስደስቱ በክርስትናም መመላለስ እንደሚቻል ማስተማራቸው ነው። አደገኛውና ለሥጋውያን ሰዎች መስህብ የሚኖረው ይህ የተቀባ ሃይማኖተኝነት ነው።

ይህ ከክርስትና መሠረታዊ ትምህርት የራቀ ነው። ጸጋ መብዛቱ እውነት ነው፤ ሮሜ 5። ነገር ግን ጸጋ በዛ ብለን በኃጢአት እንድንጫወት የተፈቀደልን ሰዎች አይደለንም፤ ሮሜ 6፥1 ይህን ይነግረናል። እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?

5. ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ። ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ። መካድ አላውቅም፤ ምንም ግንኙነትና ዝምድና የለኝም ማለት ነው። እንቢ፥ አሻፈረኝ ማለትም ነው። ለምሳሌ፥ በዕብ. 11፥24 ሙሴ እንቢ አለ የሚለው ቃል ከዚህ አንድ ነው። ይህ ክሕደት ሳያውቁ ቀርተው ተባባሪ መሆን ሳይሆን አውቆ፥ አመዛዝኖ፥ አሰላስሎ እንቢ ማለት ነው። ይህ ውጤቱ ነው።

ክርስቶስ የተገለጠበት ቋንቋ ሥልጣኑን የሚያሳይ ነው። አዳኝና መድኃኒት ሳይሆን ንጉሥና ጌታ ነው የተባለው። መንፈሳዊ መገዛት ብቻ ሳይሆን በሥጋቸው ለሥልጣኑ ፍርሃት የሌላቸውም ሰዎች ናቸው። ሐሰተኞች ሾልከው የገቡ የውስጥ ከሐዲዎች ብቻ ሳይሆኑ በተግባራቸውም ከሐድያን ናቸው። ሐሰተኞች በፍጻሜያቸውም ከሐዲዎች ናቸው። ክሕደታቸው የልብም የተግባርም ነው።

ማስጠንቀቂያዎች፤

ሀ. የወደቁ እስራኤል ምሳሌነት

5፥ ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብፅ አገር ሕዝቡን ሊድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

ይሁዳ እየጻፈ ያለው ስለ ሐሰተኞች ነው። እነዚህ ሐሰተኞች በብዙ ቃላትና መግለጫዎች ተገልጠዋል። ይሁዳ ከስማቸው ይልቅ ግብራቸውና መልካቸው ላይ ያተኮረ ማስጠንቀቂያ ነው የጻፈው። ይህ ባለፈው ያልኩትና መደገም የተገባው እውነት ነው።

ሐሰተኞችን ለመግለጥ ይሁዳ ከተጠቀመባቸው የማስጠንቀቂያ ምሳሌዎች አንዱ ከግብጽ የወጡና ነገር ግን፥ ወደ ተስፋዋ ምድር ያልገቡ አይሁድ ናቸው። ይህ ታሪክ ሰፊና ተወዳጅ የሆነ ከብሉይ ኪዳን ታሪኮች አንዱ ነው። ጠቅላላው ታሪክ ከአሪት ዘጸአት እስከ መጽሐፈ ኢያሱ ድረስ የሚገኙትን አምስት መጻሕፍት የሚያካልል ነው። አንባቢዎቹን ሲጠቅስ፥ “ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ” ሲል ተደራሲዎቹ ታሪኩን የተረዱ፥ ያነበቡ፥ የተማሩ መሆናቸውን ያመለክታል። የዘጸአት ታሪክ የሚያውቁት ታሪክ ነው።

ይሁን እንጂ ማስተዋል ያለባቸው ነገር ስላለ ‘ላሳስባችሁ እወዳለሁ’ በማለት ያንንም ያሳስባቸዋል። እነዚያ የይሁዳ የመጀመሪያዎቹ የመልእክቱ ተቀባዮች እና አንባቢዎች ልክ እንደ ዘመናችን ብዙ ክርስቲያኖች ሁሉ አይሁድ ሁሉ (ከበጣም ጥቂቶች በቀር) ከግብጽ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደገቡ ይመስላቸዋል።

እስራኤል ከግብጽ ሲወጡ ተቆጥረው ነበር። በዘኍልቍ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ቆጠራ ተደርጎአል። አንዱ ሲወጡ ሁለተኛው፥ ከ40 ዓመታት በኋላ ሊገቡ ሲሉ። ለዚህ ነው መጽሐፉ ዘኍልቍ የተባለው፤ ቁጥሮች እንደማለት ነው።

ጠቅላላ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ አንድ ንጽጽር ብቻ ለማሳየት እወድዳለሁ። በዘኍ. 1፥ 45-46 የወጡት ሰዎች ቁጥር ተጽፎአል፤ እንዲህ ተብሎ፥ ከእስራኤልም ልጆች የተቈጠሩት ሁሉ፥ በየአባቶቻቸው ቤቶች፥ ከሀያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያሉት፥ ወደ ሰልፍ የሚወጡት ሁሉ፥ የተቈጠሩት ሁሉ ስድስት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ ነበሩ። (603,550)።

ይህ ጠቅላላው የወጣው ሕዝብ ሳይሆን ዕድሜያቸው ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ወንዶች ብቻ ናቸው። ይህ የመጀመሪያው ዙር ቆጠራ ነው። ሁለተኛው ዙር ቆጠራ በዘኁ. 26 ይገኛል። እዚያም የተቆጠሩት ከ20 ዓመት በላይ ያሉት ናቸው። ቁጥር 51 ቁጥራቸውን ይነግረናል እንዲህ ሲል፥ ከእስራኤል ልጆች የተቈጠሩት እነዚህ ናቸው፤ ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ ነበሩ። (601,730)።

ይህ ከላይ ሲታይና ሲሰላ 2ሺህ የማይሞሉ ሰዎች ብቻ የሞቱ ያስመስለውና ከሞተ ተረፍ፥ ከሞላ ጎደል ብዙም ልዩነት የሌለው ይመስላል። ነገር ግን ዘኁ. 14፥20-38 ላይ ሌላ አስደንጋጭ ታሪክ እናገኛለን። ያ ታሪክ የሚነግረን ከእነዚያ 603,550 ጎልማሶች ውስጥ በሕይወት ተርፈው ወደ ተስፋዋ ምድር የገቡት ሁለት ብቻ ናቸው፤ ኢያሱ እና ካሌብ። የቀሩት በሙሉ በምድረ በዳ አለቁ፤ ሞቱ። በሁለተኛው ዙር ቆጠራ የተቆጠሩት ሰልፈኞች ቁጥር 601,730 የሆነው በመጀመሪያው ዙር ቆጠራ ከ20 ዓመት በታች የነበሩና በምድረ በዳው ጉዞ በመጀመሪያዎቹ 20 ዓመታት የተወለዱት ሰዎች ናቸው። ይህ ጠቅላላው ታሪክ በአጭሩ ነው። ያልገቡቱ ያልገቡበት ምክንያት ባለማመናቸው ጠንቅ ነው። ዕብ. 3፥16-19፤ 4፥6-7 ይህንን ይገልጣል። ጳውሎስም በ1ቆሮ. 10 ይህንን እውነት ጽፎአል። በቁ. 5 ላይ እንዲህ ይላል፥ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፥ በምድረ በዳ ወድቀዋልና።

ይሁዳ፥ “ጌታ ከግብፅ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ።” በማለት የሚናገረው ይህንን እውነት ነው። የወጡት ሁሉ አልገቡም። ለምን? ስላላመኑ። ስላልታዘዙ። እግዚአብሔርን ስለተፈታተኑ። እልከኞች ስለሆኑ። ስላስቆጡት። እነዚህ ሰዎች ድነዋል? ከግብጽ ወጥተዋል? አዎን። ግን በመንገድ ጠፉ።

የይሁዳ ማስጠንቀቂያ ግልጽ ነው። መውጣት አንድ ነገር ነው። መኖር ግን ሌላ ነው። ሐሰተኞች አስተማሪዎች ከክርስቶስ ጋር ተጣብቆ የመጓዝን፥ እርሱን የመከተልን፥ መስቀልን የመሸከምን፥ የደቀ መዝሙርነትን ዋጋ የማያሳዩ አንጠባጣቢዎች ናቸው። ከግብጽ ግር ብሎ የወጣውን ሕዝብ ብዛት ያየ ይደነቃል። ከ600ሺህ ጎልማሶች 2 ብቻ እንደገቡ ሲታሰብ ግን ያስደነግጣል።

ከግብጽ ባርነት ወጥቶ ወደ ተስፋዋ ምድር የድል ሕይወት ለመግባት የሚጠይቀው ግርግር ሳይሆን መጽናት ነው። የብዙሃን ድምጽ ሳይሆን በተስፋ ሰጪው ቃል በመታመን መገስገስ ነው። ወደ ግብጽ እንመለስ ሳይሆን ጸንተን እንጓዝ ነው። መጣበቅና ዋጋ መክፈል ቀላል አይደለም። ሰፊው ሕዝብ አደገኛ ነው። የሕዝብ ሰው

መሆንም አደጋ ነው። በምድረ በዳ ወድቀው የቀሩት ደፋቀና እያሉ ወደ ተስፋ ከማዝገም ይልቅ ወደ ግብጽ መመለስ የመረጡት ናቸው። ሥጋቸው ከግብጽ ወጣ እንጂ ልባቸው ከእትብታቸው ጋር በግብጽ ነው የተቀበረው። እነዚህ መናን 'ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ' የሚሉና፤ 'በግብፅ ያለ ዋጋ እንበላው የነበረውን ዓሣ፥ ዱባውንም፥ በጢኹንም፥ ኩራቱንም፥ ቀዩንም ሽንኩርት፥ ነጩንም ሽንኩርት እናስባለን' እያሉ ለሀጫቸውን የሚያዝረበርቡ ናቸው። የጌታ ነጻ ሆኖ ለጊዜው መና ከመብላት ባሪያ ሆኖ ያለዋጋ ዱባና ሽንኩርት የሚመኙ ናቸው። ባርነትንም ነጻነትንም በዋጋ መተመን የተሳናቸው የዕለት ጉርሰኞች ናቸው።

ሐሰተኞች ነቢያት ተከታዮቻቸውን በመንገድ አዝረክርከው የሚፈጁት ሰማያዊውን በማስጣልና ምድራዊውን በማስናፈቅ ነው። መብል፥ መጠጥ፥ ልብስ፥ መኪና፥ ቤት፥ ሹመት፥ ጤንነት፥ ገንዘብ፥ ብር፥ ወርቅ፥ ከዚህ አያልፍም። ዛሬም ሐሰተኛ ነቢያት የሚረጩትን 'ጠበል' እና የሚበትኑትን ሻሞ ብንመረምር ዱባ፥ ሽንኩርት ነው። መንገድ አዝረክርኮ የሚያስቀር። እዳር የማያደርስ። እንጠንቀቅ።

ለ. የወደቁ መላእክት ምሳሌነት

6፥ መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እሰራት ከጨለማ በታች እሰከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል።

ቀጥሎ ይሁዳ ስለ ሐሰተኞች ምሳሌ አድርጎ ምስክር የጠራው ስፍራቸውን የለቀቁ መላእክትን ነው። የይሁዳ መልእክት በግልጽ የማናገኛቸውን ነገሮች በማውሳት የታወቀ አጭር መጽሐፍ ነው። አንዱ ስፍራ ይህ ነው። ይህ ጥቅስ ስፍራቸውን ለቅቀው በእስራት ስለሚገኙ መላእክት ይናገራል። በጣም ግልጽ አይደለም። ይህ መኖሪያን መተው እና አለቅነትን አለመጠበቅ በዘፍ. 6 ካለው የእግዚአብሔር ልጆች እና የሰው ሴቶች ጋር የተደረገው የዝሙት ኃጢአት እንደሆነ ይገምታሉ። ቁጥር 6 ከቁጥር 7 ጋር ስለሚያያዝም ያ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። መላእክት ሊያገቡና ሊጋቡ ስለማይችሉ ያ ሊሆን አይችልም። ይህ ከሆነና ያንን ኃጢአት ያደረጉት ታስረዋል ቢባል ያልታሰሩት ያንን ከማድረግ የሚከለክላቸው የለምና ሰውና አጋንንት እየተጋቡና እየተዋለዱ ሊኖሩ በቻሉም ነበር። ቃሉም መኖሪያቸውን መተዋቸውን እንጂ መልአክነታቸው ትተው ሰውነትን መላበሳቸውን አይናገርም።

ስለ መላእክት ጥቂት ነጥቦችን እናስተውል። መላእክት መናፍስት የሆኑ ፍጡራን ናቸው። በዘጸ. 20፥11 እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ የፈጠረው በስድስት ቀን መሆኑ በግልጽ ስለተጻፈ መላእክትም በእነዚያ ቀናት የተፈጠሩ ፍጡራን ናቸው። ኢዮ. 38፥

6-7 አጥቢያ ኮከቦች በአንድነት ሲዘምሩ፥ የእግዚአብሔርም ልጆች ሁሉ እልል ሲሉ፥ መሠረቶችዋ በምን ላይ ተተክለው ነበር? የማዕዘንዋንስ ድንጋይ ያቆመ ማን ነው? የሚለው መላእክትን መጥቀሱ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ስለሚጠቅሱ መላእክት ምናልባት በመጀመሪያው ወይም በሁለተኛው ቀን ሳይፈጠሩ አልቀሩም።

ሕዝ. 28 ጥንግ ትርጉም ያለው ክፍል ነው። በተመሳሳይ ጊዜ በማመሳሰል ስለ ሁለት አካላት የሚናገር ነው። በቀጥታ ስለ ጢሮስ ንጉሥ የሚናገር ሲሆን ከጀርባው ሆኖ የጢሮስን ንጉሥ ስለሚያሾረው ስለ ሰይጣንም ይናገራል። በተለይ በቁ. 13-15 እንዲህ ይላል፤ በእግዚአብሔር ገነት በዔድን ነበርህ፤ የከበረ ዕንቁህ ሁሉ፥ ሰርድዮን፥ ቶጳዝዮን፥ አልማዝ፥ ቢረሌ፥ መረግድ፥ ኢያስጲድ፥ ሰንፔር፥ በሉር፥ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፥ ወርቅ፥ ልብስህ ነበረ፤ የከበሮህና የእንቢልታህ ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፤ በተፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው ነበር። አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ፤ በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ። ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ።

ይህ ክፍል የሚያሳየን ከተፈጠረ በኋላ የነበረበትን ስፍራ (የእግዚአብሔር ገነት ዔድን)፥ የከበረ አልባሳቱን፥ የተፈጠረበትን ዓላማ፥ በደል ተገኝቶበት መውደቁንና ይህ በደል እስኪገኝበት ድረስ በመንገዱ ፍጹም እንደነበረም ይናገራል። በደሉ ምን እንደሆነ ሕዝቅኤል አልገለጠውም። ሆኖም በዔድን ገነት መመላለሱና ወድቆ እዚያው የነበሩትን የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አዳምና ሔዋንን እንዳሳተ ተጽፎልናል። በኢሳ. 14 ግን ትንሽ ፍንጭ እናገኛለን። ይህ ክፍል ስለ ሰይጣን ውድቀት መነሻ አሳብ ተደርጎ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች የሚጠቀስ ሌላ ክፍል ነው።

ኢሳ. 14፥12-15 እንዲህ ይላል፤ አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ! አንተን በልብህ፦ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ።

ከላይ ያየነው ሰይጣን ፍጡር መሆኑንና በፍጹምነት ሄዶ መውደቁን ነው። አወራረዱና አወዳደቁን ወይም መቼ መውደቁን አይናገርም። በዔድን ገነት ሔዋንን እና አዳምን ያሳተው እርሱ ነውና ገና ቀድሞውኑ፥ ከነአዳም ውድቀት ቀድሞ ወድቆ ነበር ማለት ነው። እነ አዳም ከመውደቃቸው በፊት በዔድን ገነት ምን ያህል ዘመን እንደኖሩ አይታወቅም። መውደቁ ግን ከዚያ በፊት ነው። ዮሐንስ በራእዩ ያየው በራእ. 12፥3-4

ያለው የሰማይን ከዋክብት ሲሶ (አንድ ሦስተኛ) በጅራቱ ይዞ የወረደው ይህ የወደቀው አጥቢያ ኮከብ ሳይሆን አይቀርም። ቀደም ሲል ኢዮብ ውስጥ ያነበብነው አጥቢያ ኮከቦች ሲዘምሩ የተባለውን ያስታውሷል። ይህ የቀድሞውን አወዳደቅ ያሳይ ከሆነ ሲወድቅ ከከዋክብት (ከመላእክት) ከሦስት አንዱን አስቶ አስከትሎ ነው የወረደውና የወደቀው።

ጌታ በሉቃ. 10፥18 እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። ያለው ያንን ሳይሆን አይቀርም። አወዳደቁ ደማቅና ፈጣን ነው። ደግሞም እጅግ ከፍ ካለ ከፍታ በጣም ዝቅ ወዳለ ዝቅታ ነው የወደቀው። የወደቁት መላእክት አንድ ዋና ያሳታቸው አለቃ ይኑራቸው እንጂ ምን ያህል እንደሆኑ ቁጥራቸው አይታወቅም። የመላእክት ቁጥር እጅግ ትልቅ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ቦታዎች ይመሰክራል። በ1ጢሞ. 3፥6 ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪነት ሲጽፍ፥ በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። ብሎአል። ይህ የወደቀበትን ውድቀት መነሻ ያመለክታል። በ2ቆሮ. 11፥14 ደግሞ ስለ ጥልቅ አሳቸነቱ ሲጽፍ እንዲህ ብሎአል፤ ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። ሰይጣን ሲያስት የነበረውን ማንነቱን መምሰልና ማስመሰል በሚገባ ይችላል።

ወደ ይሁዳ ስንመለስ፥ ይሁዳ እነዚህን የወደቁ መላእክት የገለጠበት ቋንቋ ገላጭ ነው። ደግሞም ንጽጽራዊ ነው። እነዚህ መላእክት መኖሪያ ነበራቸው፤ ትተውታል፤ ግን ከጨለማ በታች በሌላ መኖሪያ ስፍራ ተጠብቀዋል። ይህ የስፍራ ክስረት ነው። ደግሞም አለቅነት ነበራቸው፤ አልጠበቁትም፤ ግን እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ታስረው ፍርደኛ ሆነው ይጠበቃሉ። ይህ ደግሞ የሥልጣን ክስረትና ውርደት ነው። መላእክት ልክ እንደ ሰዎች ሁሉ የራሳቸው ፈቃድ ያላቸው ፍጡራን ናቸው። ፈቃድ እግዚአብሔር ከፍጡሮቹ ለሰዎችና ለመላእክት የሰጠው ድንቅ ስጦታ ነው። እግዚአብሔር በሊሎች ፈቃድ ላይ ስለማይሰለጥን ራሳቸው ባለቤቶቹ ቅጣታቸውን ይቀበላሉ።

ይሁዳ እየጻፈ ያለው ስለ ሐሰተኞች ነው። እነዚህ ሐሰተኞች በብዙ ቃላትና መግለጫዎች ተገልጠዋል። ይሁዳ ከስማቸው ይልቅ ግብራቸውና መልካቸው ላይ ያተኮረ ማስጠንቀቂያ ነው የጻፈው። ይህ ባለፈው ያልኩትና መደገም የተገባው እውነት ነው። ይሁዳ የጻፈው ከወደቁትና ስፍራቸውን ከተዉት መላእክት እዚህ የተጠቀሱት ታስረው እስከ ፍርድ ቀን ድረስ የሚጥጠበቁ መኖራቸው ነው። እግዚአብሔር የሚቀጣ አምላክ ነው። ስፍራቸውን የተዉ መላእክት ተቀጥተዋል፤ እንደዚሁ ስፍራቸውን የተዉ ሰዎችም መቀጣታቸው የማይቀር ነው። በዚህ ጥቅስ የይሁዳ መልእክት ይህ ነው።

ሌላው ማስጠንቀቂያ፥ እነዚያ መላእክት አስቀድሞ የከብር ስፍራ እና አለቅነት የነበራቸው መሆናቸው ቅጣታቸውን አላስቀረውም። ባለፈው በቁጥር 5 እንዳየነው የአሁን መጣበቂያ እንጂ የቀደመ መታወቂያ ጥቅም የለውም። ሰይጣን ራሱ የወደቀበትን ውድቀትና ያጣውን እጦት በሚሊዮን አባዝቶ በዘመናት ውስጥ ሲያደርግ ኖሮአል። እያደረገም ነው። ሐሰተኞች ነቢያትና የሐሰት አስተማሪዎች ልክ ስፍራውን እንደተወው እንደ ሰይጣን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካዘጋጀው ዘላለማዊ ፍስሐ ራሳቸውን የጣሉ፥ ስፍራቸውን የተዉና፥ ሌሎችንም የሚያስተዉ ሰዎች ናቸው። አሳቾች እያሳቱ ከስፍራ የሚያላቅቁ፥ ከከብር የሚያንድሉ፥ ወደ ፍርድ እየተነዱ የሚነዱ ሰዎች ናቸው።

ሐ. የሰዶምና ገሞራ ምሳሌነት

7፥ እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።

ቀጥሎ ይሁዳ ስለ ሐሰተኞች ምሳሌ አድርጎ ምስክርና የቅጣት ምሳሌ የጠራው ሰዶምና ገሞራን ነው። ‘እንደ እነርሱ’ ሲል በቁ. 6 እንደተጻፉት እንደ መላእክቱ ማለቱ አይደለም። መላእክቱ መኖሪያቸውን መተዋቸውን እንጂ መልአክነታቸው ትተው ሰውነትን መላበሳቸውን አለመሆኑን ባለፈው አይተናል። እዚህ፥ ‘እንደ እነርሱ’ ሲል እንደራሳቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች ማለቱ ነው።

የሰዶምና ገሞራ ቅጣት ታሪክ በዘፍ. 19 የተጻፈው ነው። ከዚያ በፊት ግን በዘፍ. 13፥5-13 አብርሃምና ሎጥ የተለያዩበት ታሪክ ተጽፎአል። የአብርሃምና የሎጥ ጥል በከብቶቻቸው ብዛት ምክንያት ነው። ሲለያዩ ሎጥ የመረጠው አገር ሰዶምና ገሞራ ያሉበት አገል ነው። ቁጥር 10 እንዲህ ይላል፤ *ሎጥም ዓይኑን አነሣ፥ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ፤ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ከማጥፋቱ አስቀድሞ እስከ ዞዓር ድረስ እንደ እግዚአብሔር ገነት በግብፅ ምድር አምሳል ነበረ።* አገሩ ድንቅ ነው። እንደ ግብጽ ምድር አምሳል ሲል ልምላሜውን፥ እንደ እግዚአብሔር ገነት ሲል ከልምላሜው ጋር ውበቱንም መናገሩ ነው።

አገሩ ውብ ነው፤ ሰዎቹ ግን መልካም አልነበሩም። እንደ እግዚአብሔር ገነት በመሰለ በመልካም አገር ከሚኖሩ ክፉ ሰዎች ይልቅ ባረረ ምድረ በዳ የሚኖሩ መልካም ሰዎች

እጅግ የተሻሉ ናቸው። ቁ. 13 ስለ ሰዎችእንዲህ ይላል፤ *የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ።*

በሕዝ. 16፥49-50 የሰዶም ኃጢአት እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ እነሆ፥ የእኅትሽ የሰዶም ኃጢአት ይህ ነበረ፤ ትዕቢት እንጀራን መጥገብ መዝለልና ሥራ መፍታት በእርስዋና በሴቶች ልጆችዋ ነበረ፥ የችግረኛውንና የድሀውንም እጅ አላጸናችም። ኰርተው ነበር በፊቴም ርኩስ ነገር አደረጉ፤ ስለዚህ ባየሁ ጊዜ አጠፋኋቸው።

እንዲያ ገነት በመሰለ ለምለምና ሀብታም ምድር በመኖራቸው አመስጋኝና የሰጣቸውን አምላክ አመስጋኝ መሆን ሲገባቸው ያለ ቅጥ እቀማጠሉ፤ ባለጉ፤ መዝለልና ሥራ መፍታት፥ መኩራትና ርኩሰትን መፈጸም ተግባራቸው ሆነ። ርኩሰታቸው ደግሞ በዘፍ. 19 የተጻፈው ነው። በዘፍ. 19 ሁለት እንግዳ የሆኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች ታሪኮች ተጽፈዋል። ሁለተኛው የሎጥ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ጋር የመተኛታቸው ታሪክ ሲሆን የመጀመሪያው የሰዶም ሰዎች ወደ ሎጥ ቤት የገቡትን ሰዎች አስገድዶ ለመገናኘት ያደረጉት ሙከራ ነው። ይህ ሰዶማዊነት እየተባለ በኋላ የተጠራው የተመሳሳይ ጾታ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው።

ዘፍ. 19፥4-5 *እንዲህ ይላል፤ እንዲህ ይላል፥ ገናም ሳይተኙ የዚያች ከተማ የሰዶም ሰዎች፥ ከብላቴናው ጀምሮ እስከ ሸማግሌው ድረስ በየሰፍራው ያለው ሕዝብ ሁሉ፥ ቤቱን ከበቡት። ሎጥንም ጠርተው እንዲህ አሉት፦ በዚህ ሌሊት ወደ ቤትህ የገቡት ሰዎች ወዴት ናቸው? እናውቃቸው ዘንድ ወደ እኛ አውጣቸው።*

ወደ ሎጥ የመጡት የሰዶም ሰዎች፥ ‘ሰዎች’ ተብለዋል። ወንዶች ናቸው። ወደ ቤቱ የገቡትን ሰዎች የጠየቁበት ቃልም፥ ‘ሰዎች’ የሚል ነው። በእርግጥ እነዚህ በሎጥ ቤት የትጠለሉት ሰዎች ሳይሆኑ መላእክት ናቸው። ግን የሰዶም ሰዎች የመሰሉአቸው ወንዶች ሰዎችን ነው። እናውቃቸው ዘንድ ማለት በብሉይ ኪዳን የጨዋ ቋንቋ በግብረ ሥጋ መገናኘት ማለት ነው። እዚህ የሚታየው ወንዶች ወንዶችን በግብር ለማወቅ መምጣታቸውን ነው።

ጳውሎስ እንዲህ ስላሉት ሰዎች በሮሜ 1፥18-32 በዝርዝር ጽፎአል። ወንዶች ከወንዶች ጋር፥ ሴቶችም ከሴቶች ጋር የባሕሪያቸውና የተፈጥሮአቸው ተቃራኒ በሆነ መንገድ መገናኘታቸው እግዚአብሔርን ካለማወቅ ሳይሆን አውቆ ካለማክበር የተነሣ ነው። እነዚህ ሰዎች አውቀውና ወድደው የተፈጥሮን ሕግና የእግዚአብሔርን ቃል በመጣሳቸው ለማይረባ አእምሮ የተሰጡ ሆኑ።

የሰዶም ሰዎች ሰዶማዊ እርምጃ ለከተማዋ በእሳትና ዲን ተቃጥሎ መገልበጥ ምክንያት የሆነ ኃጢአት ነው። ዘፍ. 19፥24-25 እንዲህ ይላል፤ *እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያንም ከተሞች፥ በዙሪያቸው ያለውንም ሁሉ፥ በከተሞቹም የሚኖሩትን ሁሉ፥ የምድሩንም ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ።* ሰዎቹም፥ አገሪቱም ከነሙሉ ውበቷ ወደሙ።

ዛሬም ሰዶማዊነት እና ከዚያ ጋር የተያያዙ ከተፈጥሮ ሕግ እና ከእግዚአብሔር ቃል የራቁ ግብረ ሥጋዊ ግንኙነቶች በዓለማችን ብዙ አገሮች ሕጋዊነትን እየተቀዳጁ ይገኛሉ። በጣም የሚታወቅበት ስም LGBT ነው። አሁን QIA2 የሚሉ ተጨምረውበታል። LGBTን አመሳቅዬ GLBT (ወይም ግልብጥ) ብዬ ስለ ግልብጥ ጋብቻ አደገኛና መሰርይ አዝማሚያና አካሄድ የጻፍኩትን ከዚህ ያግኙ፤ http://books.good-amharic-books.com/EzMag031.pdf

ይሁዳ እየጻፈ ያለው እምነትን ስለሚሸረሽሩ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች እና ስለ ቅጣታቸው ነው። የሰዶማውያን እና የሰዶም ቅጣት የራሳቸው ብቻ ቅጣት ሳይሆን ምሳሌያዊ ቅጣትም ነው። አመልካች ቅጣትም ነው። የሐሰት ነቢያትን እና አሳች አስተማሪዎችን ቅጣት የሚያመለክትም ነው። የሰዶምና የዙሪያዋ ከተሞች ቅጣት እሳት ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ እሳትም ነው። 'በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል' ነው ይሁዳ ያለው። እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ አለማወቅ ምድራዊ፥ ሥጋዊ፥ አካላዊ ቅጣት ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊ ፍርድም አለበት።

7፥ እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።

የከሐድያን መልክ

ሀ. ተሳዳቢነት

8፥ እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉ።

9፥ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር፦ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም።

10፥ እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥ አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ።

እንዲሁም እነዚህ ደግሞ በማለት ነው የሚጀምረው። እነዚህ የተባሉት ይሁዳ እያስጠነቀቀ የጻፈባቸው ሐሰተኞቹ ናቸው። እነዚህ ሰዎች እያለሙ ሥጋቸውን ያረከሳሉ ሕልምና መርከስ መያያዛቸው ወይም እያለሙ ሥጋቸውን ማርከሳቸው ከላይ ከተጠቀሰው የሰዶምና ገሞራ ወሲባዊ ርኩሰት ጋር ሊገናኝ ይችላልም። ይህ እዚህ የተጠቀሰው መርከስ በዮሐ 18፥28 እንደተጠቀሰው ያለ ለሕግ ወይም ወግ ሥርዓት መርከስ ሳይሆን በቲቶ 1፥15 እና ዕብ. 12፥15 እንዳለው ውስጣዊ ርኩሰት ነው። ይህ የይሁዳ ቃል የተጻፈባቸው 4 ጥቅሶችም እነዚህ ብቻ ናቸው።

ሕልም ብዙውን ጊዜ በአእምሮአችን ጓዳ የተደበቀ የእውን ማንነታችን መገለጫ ነው የሚሉ ስነልቡናውያን አሉ። የጥልቅ እንቅልፍ ምልክት ነውም ይላሉ፤ መክ. 5፥3 በሥራ ብዛት ይታያል ማለቱ ከድካም ጋርም ያያይዘዋል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በሕልም ብዙ ጊዜ ተናግሮ ስለነበር ሕልም ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ የሚገምቱም አሉ። መንፈስ ቅዱስ ከወረደና በአማኞች ውስጥ መኖር ከጀመረ ወዲህ ለመለኮታዊ አመራር ሕልም አለመታየቱን ደግሞ እናስተውል። መመሪያችን ቃሉም በእጃችን እንዳለ አንዘንጋ። ስለዚህ ሕልም ሁሉ ከጌታ መስሎን ቅዠታችንን ሁሉ ልናስፈታ አንጨነቅ።

የእነዚህ ሕልም ከርኩሰት ጋር መያያዙ የሕልም ሕልም ብቻ ሳይሆን የእውን ሕልምም ሊሆን እንደሚችል በቀላሉ መገመት ይቻላል። ሕልም ሲባል ተኝተው በልቡና ዓይን የሚያዩት ብቻ አይደለምና። ጠሊቅ ምኞትም ሕልም ይባላል። እንዲህ ከሆነ የነዚህ ሰዎች ሕልም ሥጋን የሚያረክስ ነው። ምንድርን ነው ሥጋን የሚያረክስ? ብለን ስንጠይቅ ሥጋን የሚያረክስ መንፈሳዊ ወይም ከእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር ሁሉ ነው። ስሜታዊ፥ ሥጋዊ፥ ምድራዊ፥ ኢጋንንታዊ፥ ጊዜያዊ፥ ጠፊ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የማይሸት፥ እግዚአብሔር የማይሸት፥ ለእንደዚያ ያለው ነገር ሲሉ፥ ይህን ለማግኘት ሲሉ፥ ይህን እያለሙ፥ እየተመኙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ።

የእነዚህ ሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ቃላቸውም የረከሰ ነው። በእነዚህ ሦስት ጥቅሶች ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰው ጉልህ ቃል መሳደብ ነው። መሳደብ በ3ቱም ጥቅሶች ውስጥ ይገኛል። ሥልጣን ያላቸውንም፥ የማያውቁትንም ይሳደባሉ። ይሁዳና 2ጴጥሮስ በጣም ተቀራራቢ መልእክቶች ናቸው። ጴጥሮስም ይህን ሲል፥

2ጴጥ. 2፥9-12 ተመሳሳይ ነገር ይላል፤ ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፥ በደለኞችንም ይልቁንም በርኩስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል። ደፋሮችና ኩሩዎች ሆነው ሥልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ አይንቀጠቀጡም፤ ዳሩ ግን መላእክት በኃይልና በብርታት ከእነርሱ ይልቅ ምንም

ቢበልጡ በጌታ ፊት በእነርሱ ላይ የስድብን ፍርድ አያመጡም። እነዚህ ግን ለመጠመድና ለመጥፋት በፍጥረታቸው እንደ ተወለዱ አእምሮ እንደ ሌላቸው እንስሶች ሆነው፥ በማያውቁት ነገር እየተሳደቡ በጥፋታቸው ይጠፋሉ፤

ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር፦ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም። ይህ የሙሴ ሥጋ ታሪክ እና የተከራከሩበት ጉዳይ ምንነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም። ምናልባት ዕርገተ ሙሴ ወይም ኪዳነ ሙሴ የተባለ የአፅቅሪፋ መጽሐፍ አለ፤ እዚያ ውስጥ የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም ይባላል። ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ጌላስዮስ እና አርጌንስ ይህን የይሁዳን ጥቅስ ከዚህ መጽሐፍ ጋር አያይዘው ጠቅሰውታል። ግን አሁን በሚገኝበት መልኩ ታሪኩ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አይገኝም፤ ምናልባት እነ አርጌንስ ከጠቀሱበት መልኩ ተለውጦ ወይም እስከ ጭራሹ ጠፍቶ ሳይሆን አይቀርም።

የይሁዳ ይህን የጻፈው በትውፊት ተደግፎ ይሁን ወይም ይህን ጽሑፍ አንብቦ ባናውቅም፥ ይሁዳ ይህን ጽሑፍ ጠቅሶትም ከሆነ መጥቀሱ የተጠቀሰበትን ምንጭ ቀኖናዊ ሊያደርገው አይችልም። ይሁዳ ወይም ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች ታሪካዊ ተአማኒነት ያላቸውን ምንጮች መጥቀሳቸው እነዚያን የምንጭ ጽሁፎች መለኮታዊ ምስክርነትን አያቀዳጃቸውም። ወይም ከቅዱሳት መጻህፍት ተራ ሊሰለፉ መብት አይቸራቸውም። ለምሳሌ ጳውሎስ በሐዋ. 17፥28 ለአቴና ሰዎች ሲናገር የራሳቸውን ባለ ቅኔ መጥቀሱ ወይም በቲቶ 1፥12 የቀርጤስ ሰዎች ነቢይ የሆነ ሰው የተናገረውን ሲጠቅስ እነዚያ ምንጮ ከተአማኒነታቸው የተነሣ ተጠቀሱ እንጂ ቅዱሳት መጻፍትሊሆኑ ተገባቸው ማለት አይደለም።

ስድብ የማጥላላት፥ የማንቋሸሽ፥ የመናቅ፥ የማዋረድ ቃል ነው። ስድብ የአፍ መተላለፍ ብቻ ሳይሆን የትዕቢትና የእብሪት ምልክት ነው። ሚካኤል ግን የስድብን ቃል ሊናገር አልደፈረም። ጌታ ይገስጽህ አለው እንጂ። ሚካኤል ከመላእክት አለቆች አንዱ ነው። ሚካኤል ሰይጣን እንዴት እንደወደቀ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ ግልጽ ነው። ሰይጣን ራሱም የወደቀው በልብ እብጠት ነው። ራሱን ያለ ቅጥ ከፍ ሲያደርግ እግዚአብሔርን ማቃለሉና መሳደቡ መሆኑን ሳያስተውል አይደለም ያደረገው። የከብር ስፍራ የነበረው አጥቢያ ኮከብ ከወደቀ ከአለቆቹ አንዱ የሆነው መልአክ ይህንን በእርግጥ ያውቃል። ስለዚህ እንደዚያ ላለው መተላለፍ ራሱን አሳልፎ አልሰጠም፤ አልቃጣምም።

የሐሰት ነቢያት ግን ለስድብ አፋቸው ሲከፈት ወሰን የለውም። ቁ. 10፥ *እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥ አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ።* ይላል። ሥልጣን ያላቸውን ብቻ አይደለም የሚሳደቡት። የማያውቁትንም ጭምር ነው። ሥልጣንን መቃወምና መሳደብ

የመንግሥትን ሥልጣን ሊሆን ይችላል። የቤተ ክርስቲያንንም ሊሆን ይችላል። ከሁሉም በላይ ግን የእግዚአብሔርን ነው። መሳደብ ማቃለል ነው። በቃልም ይደረጋል ያለ ቃልም ይደረጋል። ጌትነትን መናቃቸው ጌታን መናቃቸውን ሳይሆን ሥልጣንን መናቃቸውን የሚያመለክት ነው። ጌታንማ ቀደም ሲል እንዳየነው ከደውታል።

ሥልጣንን መቃወም ብቻ ሳይሆን የማያውቁትን ይሳደባሉ። ስድባቸው ስለማያውቁት ነገርም ነው። እውቀታቸው ደግሞ ደመነፍሳዊ ነው። በማስተዋል ሳይሆን እንደ እንስሶች በፍጥረታቸው ነው። ይህ ጎዶሎ እውቀት መጥፊያቸውም ነው። መጥፋት የሚለው ቃል መቆሸሽ፥ መርከስ፥ መበላሸት ነው።

ለራስ የሚሰጡት የማንነት ክብር ስድብን ሊያንጸባርቅ ይችላል። ሐሰተኞች ነቢያትና የሐሰት አስተማሪዎች ከሥልጣን ጋር ያላቸውን ግንኙነት እነርሱ ባለ ሥልጣን እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው። ከራሳቸው በቀር ሌላ ሥልጣንን አፈልጉም፤ መግዛት እንጂ መገዛትም አያውቁም። ጌትነትን ይጥላሉ፤ ሥልጣን ያላቸውን ይሳደባሉ። ተቃውሞው የቃልም የድርጊትም ነው። ይጥላሉ፤ ይሳደባሉ። ሐሰተኛ ነቢያት ስለ ሥልጣን ያላቸውን አመለካከት ለመገንዘብ ከስማቸው በፊት የሚጽፉትን፥ 'ባለ ራእይ፥ መሥራች፥ ወዘተ፥' ብቻ ሳይሆን የማኅበሮቻቸውን መዋቅር ስንመለከትም ይህን እናያለን። ብቸኛ የበላይ ባለ ሥልጣናት፥ በቡድን መሪነት የማያምኑ፥ አምባ ገነኖች ሆነው ሲገዙ በግልጽ ይታያሉ።

ለ. የቃየል መንገድ

11፥ ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል።

ይሁዳ በአጭር መልእክቱ እነዚህን ሾልከው የገቡ ከሐዲ ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎችን ማንነትና ባሕርያት ለመግለጥ ብዙ ተምሳሌቶችንና ምስሎችን ይዘረዝራል። በዚህ ጥቅስ በወዮታ ይጀምርና ሦስት ሰዎችን ከኦሪት መጻሕፍት ይጠቅሳል። ወዮታው የማይቀር ፍርዳቸውንና ቅጣታቸውን ለማሳየት ነው። የአሳቾች ቅጣት የዘገየ ይመስላል እንጂ እርግጠኛና የማይቀር ነው።

የመጀመሪያው ምሳሌ የቃየል መንገድ ነው። ቃየል በዘፍ. 4 የምናገኘው ቃየን ነው። በአዲስ ኪዳን ቃየል እየተሰኘ ነው የተጠቀሰው። የቃየል መንገድ የንዴትና የጥላቻ፥ የበቀልና የነፍስ ማጥፋት ነው። በዘፍ. 4 አቤል ከቃየን ይልቅ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት አቀረበ። በዕብ. 11፥4 አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕት በእምነት ማቅረቡ፤ እርሱ ጻድቅ መሆኑ ተጽፎአል። ዮሐንስ በ1ዮሐ. 3፥12 ቃየል ከክፉው (ሰይጣንን የሚገልጥ ቃል ነው) መሆኑን እና ሥራውም ክፉ መሆኑን ጽፎአል።

በዘፍ. 4 ታሪኩ የተጻፈው የአቤልና ቃየን ታሪክ የመሥዋዕታቸውን አቀራረብና ተቀባይነት ዘፍ. 4፥3-5 እና 8 እንዲህ ይገልጠዋል፤

ከብዙ ቀን በኋላም ቃየን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ፤ አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ። እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ። . . . ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው። በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥ ገደለውም።

መሥዋዕታቸው የተለያየ ነው። የአቤል የደም መሥዋዕት ሲሆን የቃየን የእጁ ፍሬ ነው። አቀራረባቸውም የተለያየ ነው። የአቤል መሥዋዕት የእምነት መሥዋዕት ነው። ዕብ. 11፥4 አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፥ ይላል። ዕብ. 11 የእምነት ሰዎች፥ በእምነት እግዚአብሔርን ያስደሰቱ ሰዎች የተዘረዘሩበት ምዕራፍ ነው። ስለዚህ በአቤል ውስጥ እምነት ታይቶአል።

እግዚአብሔር ከመሥዋዕታችን ይልቅ እና በፊት ማንነታችንን ነው የሚያየው እና የሚፈልገው። እንደገና በዘፍጥረት የተጻፈውን እንይ፤ እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ። ወደ መሥዋዕቱ ከማየቱ በፊት ወደ ሰውየው ያየ ይመስላል። የመሥዋዕት ተቀባይነት በሰውየው ልብ ላይ የተመሠረተ ነው። መጥፎ ሰው ጥሩ መሥዋዕትን ቢያቀርብ ቅቡል አይሆንለትም። ጥሩ ሰው ደግሞ ተገቢውን መሥዋዕት ያቀርባል። ተገቢው መሥዋዕት ኃጢአታቸውንና ኃጢአተኛነታቸውን የሚያሳስብ የስርየቱንም ደም የያዘ መሥዋዕት ነው።

ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች የሰውን ኃጢአተኛነትና ፍጹም ውድቀት፥ የክርስቶስን ደምና መስቀሉን ከፍና ደመቅ አድርገው የማይሰብኩትና የማያሳዩት እንደ ቃየን የራሳቸውን እጅ ፍሬ ለማቅረብ ሲቃጡ ነው። የሐሰተኛ ነቢያትን ዋና መልእክት

ብንፈትሽ መስቀል፥ ንስሐ፥ ትሕትና፥ የእምነት መሥዋዕት የሉበትም። እምነት ሲሉ ሌላ እምነት ነው የሚናገሩት። የሚፈጥር እምነት ይሉታል፤ ገንዘብን፥ ቁሳቁስን፥ ካለመኖር ወደ መኖር የሚያመጣ የስግብግብነት መሣሪያ ነው። የእግዚአብሔር ዓይነት እምነትም ይሉታል። እግዚአብሔር ቃሉ እንደሚፈጥር አምኖ ተናገረ ይላሉ። ሆ! ሆ! ድንቅ ነው እግዚአብሔር ሲያምን! የተሳሳተ ነጥባቸው እግዚአብሔር ቃሉ እንደሚፈጥር አምኖ ስለተናገረ እኛም ቃላችን እንደሚፈጥር ብናምን እንፈጥራለን ነው። ስለዚህ ራሳቸውን የእግዚአብሔር 'ክላስ' መደብ ወይም ምድብ አድርገው ከእግዚአብሔር ጋር አቻ ይሆናሉ። ይህ ፈተና ነው። ይህንን ፈተና ሁሉም ይወድቃል እንጂ ማንም ማለፍ አይችልም። በመጀመሪያ ሰይጣን ሞከሮት ላይነሣ የወደቀበት ፈተና ነው።

ቃየላዊ አምልኮ የራስ መታየትና የራስ መወድስ ነው። የእኔነት ዙፋን ላይ መቀመጥና ዘውድ መጫን ነው። ክርስቶስ ሳይሆን ሰዎች የሚታዩበት ነው። ሰዎች ጸልየው መልሳቸውን እንዲቀበሉ ሳይሆን ጸላዮቹ እነርሱ የሚሆኑበት ነው። ልክ ጠንቋይ ቤት ተኪዶ መጋረጃው ውስጥ ገብቶ ከጠንቋዩ ከራሱ ቃልን እንደመቀበል የመሰለ ራስ ገዘፍ ሥርዓት ነው። ትኩረቱ ሌላ ማንም ሳይሆን እነርሱ ብቻቸውን ይሆናሉ። ይህንን ከማንም ጋር አይካፈሉም፤ ለማንም አያጋሩም። ስልክ ሲደወል መላሾቹ እነርሱ ናቸው፤ ትእዛዝ የሚወጣው ዋናው ቢሮ የእነርሱ አንደበት ነው። ዙፋኑ ላይ የተቆለሉት እነርሱ ናቸው። ትሕትና ፈጽሞ የሌለበት የድፍረትና የእብሪት አካሄድ ነው። ከውጪ ትሑታን ሊመስሉ ይችላሉ። የትሕትና ቤትና መኖሪያ ግን ውጪ ሳይሆን ልብ ነው።

ቃየላዊ አምልኮ የራስ ፍሬ መደርደሪያ ላይ የሚታይበት ነው። ለምሳሌ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች (የብልጽግና ወንጌል የሚባል ወንጌል የለም፤ ያለው አንድ ወንጌል ወይም ልዩ ወንጌል ነው፤ ይህ ከልዩ ወንጌል ውስጥ የሚካተት ነው) ራሳቸውን አሳምረው በውድ ዋጋ የሚሸጡ ሰዎች ናቸው። እንደ መዥገር ምጥጥ አድርገው የሚመጥጡት የውሸት ተስፋ የሚሰጡትን መደዴውን አማኝ ሲሆን ብልጽግናው የሚገባው ግን ወደ ኪሳቸው ነው። ስለዚህ ከተራው ተከታያቸው በብዙ መቶና ሺህ እጥፍ ስለሚበለጽጉ እውነትም የእግዚአብሔር ምድብ ውስጥ የገቡ ይመስላቸዋል። ብልጽግናቸውንም በሸፍጥ ያገኙት ሳይሆን በእምነት ዘርተው ያመረቱት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ፤ ያሳስባሉም። ፍጹም የሰው ብቻ የሆነ ሃይማኖት ይፈጥሩና በከንቱ ይረቡባቸዋል።

የቃየል መንገድ በእግዚአብሔር ሳይሆን በራስ የተቀየሰ መንገድ ነው። እንደ ቃሉ የሆነ ሳይሆን እንደወረደ ያለበት መብል ነው። የሚሸከሙት መስቀል በሚነነጨበት መንቀል የተለወጠበት አኗኗር ነው። የቃየል መንገድ ጠባቧ፥ ቀጭኗና ጥቂቶች የሚሄዱባት ሳትሆን ሰፊዋና እንደልብ የሚሮጡበት፥ እንደወደደ ሳይሆን

እንደወደድኩ ተብሎ የሚፋንኑበት መንገድ ነው። በቃየል መንገድ ሄደዋልና የተባሉት ወየላቸው! የተባሉትና ወዮታ የተመደበባቸው ናቸው።

ሐ. የበለዓም ደመወዝ

11፥ ወየላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋልና በቆሬም መቃወም ጠፍተዋልና።

የበለዓም ታሪክ በዘኁ. 22-25 ባሉት አራት ምዕራፎች በዝርዝር እና 31፥15-18 ተጽፎአል። ሞቱ ደግሞ በኢያ. 13፥22 ተጽፎአል። እነዚህን ምዕራፎች እንድታነብቡ አበረታታለሁ።

በአዲስ ኪዳን ከዚህ ከይሁዳ መልእክት በተጨማሪ በ2ጴጥ. 2፥15-16 ላይ ጴጥሮስ ጠቅሶታል። እንዲህ ሲል፤ ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ፤ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤ እርሱ የዓመፃን ደመወዝ ወደደ፥ ነገር ግን ስለ መተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ።

ዮሐንስ ደግሞ በራእ. 2፥14 እንዲህ ሲል ጠቅሶታል፤ ዳሩ ግን ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበለዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋር ስላሉ፥ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ።

በለዓም በሁለት ትልልቅ በደሎች እስራኤልን የተዋጋ ሰው ነው አንዱ አልሠራለትም ሁለተኛው በሚግባ ሠርቶለታል። የመጀመሪያው ይሁዳና ጴጥሮስ የጠቀሱት በለዓም በገንዘብ ፍቅር የተጠመደና ገንዘብ ተቀብሎ ለመርገም እጅግ ሩቅ መንገድ ተጉዞ የመጣ ሰው መሆኑ ነው። የይሁዳ አሳብ ይህ ስለሆነ እመለስበታለሁ።

ሁለተኛው ዮሐንስ የጠቀሰውና በዘኁ. 25 እና 31 የሚገኘው የፌጎር ኃጢአት ነው። ይህም እስራኤል ከሞዓብ ሴቶች ጋር ያመነዘሩበትና የተቀሰፉበት ኃጢአት ነው። ይህ የሴሰኝነት ኃጢአት ሐሰተኞች ነቢያት የሚገለገሉበት ታማኝ መሳሪያቸው ነው። ይህ ራሱን የቻለ ትልቅ ርእስ ቢሆንም የይሁዳ ትኩረት የመጀመሪያው በመሆኑ ወደዚያኛው ወደ ፍቅረ ንዋይ ልመለስ።

ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል።

በለዓም እስራኤልን እንዲረግም ባላቅ የላከበት ጥሪ ይህ ነበር፤ '. . . እባክህ፥ ና ርገምልኝ፤ አንተ የመረቅኸው ምሩቅ የረገምኸውም ርጉም እንደ ሆነ አውቃለሁና ብሎ ይጠሩት ዘንድ መልእክተኞቹን ላከ። የሞዓብ ሽማግሌዎችና የምድያም ሽማግሌዎችም የምዋርቱን ዋጋ በእጃቸው ይዘው ሄዱ፤ ወደ በለዓምም መጡ፥ የባላቅንም ቃል ነገሩት።' (ዘኍ. 22፥5-7)። ይህ ሰው መራቂና ረጋሚ ነው። መመረቅና መርገም ሸቀጦቹ ናቸው። የሚረግመውና የሚመርቀውም በገንዘብ ነው።

በለዓም በመጀመሪያው ጥሪ እግዚአብሔር በግልጥ ተናግሮት አልሄደም። ሁለተኛ ሲልክበት ከፊተኛው ይልቅ የከበሩ ሰዎች ሲሆን በለዓም የተናገረው፥ "ከብርህን እጅግ ታላቅ አደርገዋለሁና፥ የተናገርኸውንም ሁሉ አደርግልሃለሁና እባክህ፥ ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ ምንም አይከልክልህ፤ እባክህ፥ ና፥ ይህን ሕዝብ ርገምልኝ" ብሎ ነበር። (ዘኍ. 22፥16-17)። በለዓም ግን ክብርን የተረጎመበት ቋንቋ የፍቅረ ንዋይ እስረኛነቱን የሚያሳይ ነው፤ "ባላቅ በቤቱ የሞላውን ወርቅና ብር ቢሰጠኝ፥ . . ." ነበር ያለው፤ (ቁ. 18)። በገንዘብ ፍቅር የታወረ ዕውር ነው በለዓም። ወደ ባላቅ ሲሄድ በመንገድ ላይ አህያዋ ያየችውን መልእክ እንኳ ማየት ያልቻለ ዕውር ነው። የገንዘብ ፍቅር የምር ያሳውራል።

ደመወዝ የሚለው ቃል የሥራ ዋጋ ነው። ስለ በለዓም በተነገረው ስፍራ የምዋርቱ ዋጋ የተባለው ነው፤ (ቁ፣ 7)። አንዳንዴ ቀድመው ይቀበሉታል፤ አንዳንዴ ቀብድ ተቀብለው ሥራው ሲያልቅ የቀረውን ይቀበላሉ፤ ብዙውን ጊዜ ከሥራ በኋላ ነው ክፍያው የሚከናወነው። በለዓም በዘመኑ በቃልቻነት ሙያው የተከበረ በመሆኑ፥ ደግሞም ውጤቱ የታወቀና በዓመታት ተፈትኖ የተረጋገጠ፥ እርሱ የረገማቸው ርጉማን፥ የመረቃቸው ምሩቃን መሆናቸው የታወቀ በመሆኑ ክፍያው እንደከናወን ውጤቱ መጠበቅ የለበትም።

'ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል' የሚለው ቃል መፍሰስ፥ መሮጥ ማለት ነው፤ እንደ ውኃ። ልክ ውኃ ዝቅ ወዳለበት፥ ቦይ ወደተቆፈረለት እንደሚፈስስ ራሳቸውን አፍስሰዋል ለቅቀዋል ማለት ነው።

ከአምስት ዓመታት አንድ የሱማሌ የባሕር ዘራፊዎች (pirates) ቡድን አንድ የሳዑዲ መርከብ ይዞ የዎጆ ገንዘብ ጠየቀ፤ 3 ሚሊዮን ዶላር ነበር የጠየቀው። ከጠረፍ ብዙ

መቶ ኪሎ ሜትር ርቀው ነው የሚደራደሩት። የመጀመሪያው 215 ሺህ ዶላር ተሰጠና ያንን ይዞ እየተመለሰ የነበረው ሰው ጀልባው ተሰበረችበት። ኋላ ሬሳው ሲንሳፈፍ ተገኘ። ሲመረመር 153 ሺህ ዶላር በላስቲክ በላስቲክ ሆኖ በኪሱም በላዩም ታስሮ ነበር። ጀልባው ከተሰበረች በኋላ ብሩን ተሸክሞ ሊዋኝ ስላልቻለ ክብደቱ አስጥሞ እንደገለው ተገምቶአል። ኋላ ሰውነቱ ተነፍቶ ሲንሳፈፍ በላዩ የታሰረው ብርም አብሮት ተንሳፈፈ። የፈለገው ነገር መሞቻው ሆነ።

የእስጳኝ ሰዎች ደቡብ አሜሪካን በተቆጣጠሩ ጊዜም ይህ ሆኖ ነበር። አንድ ከውቅያኖስ ውስጥ የተገኘ የባሕር ዘራፊ ወንበዴዎች መርከብ ስትገኝ አብሮ የተገኙ ሬሳዎችም ይህንን ያሳያሉ። ዘራፊዎቹ መርከባቸው በእሳት ስትያያዝ የወርቅ ከረጢቶቹን በወገባቸው አስረው ለማምለጥ ሞከሩ። አለመቻላቸውን የተገነዘቡት እየፈቱ ነፍሳቸውን አዳኑ። ያልፈለጉት ከወርቅ ከረጢታቸው ጋር ሰጠሙ።

በገንዘብ ሰንሰለት ተይዘው ለጠፉ ዋና ምስክር የሚሆኑ ተጠቃሾች በኢያሱ ዘመን የመነረው አካን እና ጌታውን የሸጠ ይሁዳ ናቸው። ተንባዮች ለእንጎቻ አለ ደሬ በአምልኮ ነጻነት መዝሙሩ።

ቀላዋጮች በዙ ተንባዮች ለእንጎቻ
መረቅ ላጠጣቸው ላበላቸው ብቻ
እንደመተተኛ እዚህ እዛ እያሉ
ቅልጥም ላገኙበት ይተነብያሉ
የነጻነት ውልዶች ስንቱን ያሞኛሉ
በግርግር መጥተው የተቀላቀሉ፤ የተቀላቀሉ።

ሐሰተኛ ነቢያት የሚሠሩትን ነገር የሚሠሩት ለገንዘብ ነው። ለጥቅም ነው። ሐሰተኛ ነቢያት በፍቅረ ንዋይ የተለከፉ ናቸው። በገንዘብ ፍቅር። የገንዘብ ፍቅር ደግሞ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ 1ጢሞ. 6፥10። ስለዚህ ሐሰተኛ ነቢያት ከዚህ የክፋት ስር ጋር የተቆላለፉ ናቸውና ከጥቃቅን የሰፈር ጥቅማ ጥቅሞች ጀምሮ እንደ ባላቅ እስከመሰሉ መሪዎች ድረስ ግልጋሎቶቻቸውን የሚሸጡት በገንዘብ እየተመኑና እየለኩ ነው።

ሐሰተኛ ነቢያት እንደ ትንቢት፥ የውሸት ፈውስ፥ የማይፈጸም ተስፋ፥ የትጠረምሳለህ ትደረምሳለህ አዎንታዊ ቃል፥ እና የመሳሰሉ ሃይማኖታዊ ሽቀጦች በመቸርቸር ራሳቸውን እንደ ውኃ ያፈሰሱ ቃልቻዎች ናቸው።

ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል።

መ. የቆሬ መቃወም

11፥ ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል።

ቆሬ ማን ነው? የቆሬን መቃወም ለመረዳት ወደ ብሉይ ኪዳን መጓዝ አለብን። በብሉይ ኪዳን ቆሬ የተባሉ 5 ሰዎች ይገኛሉ። ይህኛው ቆሬ በዘጸ. 6፥21-24፤ ዘኁ. 16 እና 26፤ 27፥3፤ 1ዜና. 6፥23፥38 እና በአዲስ ኪዳንም የአመጽና የተቃውሞ ምሳሌ ሆኖ በዚህ በይሁዳ ጥቅስ የተጠቀሰው ነው።

ቆሬ በሙሴ ዘመን የነበረ ከቀዓት ወገን የይስዓር ልጅ የሆነ ሌዋዊ ሰው ነው። ሌዊ ሦስት ልጆች ነበሩት፤ ጌድሶን፥ ቀዓት እና ሜራሪ ይባላሉ። ራሳቸው ሙሴና አሮን ከቀዓት ወገን የሆኑ እንበረማውያን ናቸው። በእግዚአብሔር ምርጫ ግን አሮንና ልጆቹ የክህነት ድርሻ ተሰጣቸው። ለቀዓት ልጆች የተሰጠ የመቅደስ አገልግሎት አለ። የቆሬ ድርሻ በዚያ መሳተፍ ነው። የቀዓታውያን ድርሻ በተለይ በዘኁ. 4 ይገኛል። ዘኁ. 7፥9 ለቀዓት ልጆች ግን መቅደሱን ማገልገል የእነርሱ ነውና፥ በትከሻቸውም ይሸከሙት ነበርና ምንም አልሰጣቸውም። ይላል። ምንም አልተሰጣቸውም የሚለው ሰረገሎችን ነው። ጠቅላላውን ዘኁ. 7ን አንብቡ። ለጌድሶንና ለሜራሪ ወገኖች ሰረገሎች ተሰጥተው ለቀዓት ወገን ያልተሰጠው እነርሱ የመገናኛውን ድንኳን ዕቃዎች በትከሻቸው የሚሸከሙ ሰዎች ስለነበሩ ነው። ይህ መታደል ነው። እነዚያን የከበሩ ዕቃዎች ሊፋንኑ በሚችሉ በሬዎችና ሊያዘነብል በሚችል ሰረገላ ሳይሆን (የያዛን ስብራት ያስታውሷል) የተመጠነ እርምጃ በሚራመዱ እርስ በርስ በሚነጋገሩ ሰዎች ትከሻ እንዲጓዝ ማድረጉ የእግዚአብሔር ጥበብ ብቻ ሳይሆን ለሰዎቹም ክብር ነው። ቆሬ ይህንን ክብር ከታደሉት አንዱ ነበር። ኋላ እኮ ሊቃ ካህናቱ እንኳ በዓመት አንዴ ብቻ ገብቶ የሚረጭበትን ታቦት ቆሬ ከወንድሞቹ ጋር በትከሻው ሊሸከም ታድሎ ነበር።

በዘኁ. 16 ግን ሌላ ታሪክ እናነብባለን። ምዕራፉን በሙሉ ይነበብ። ቆሬ ከሮቤል ነገድ ከሆኑ ዳታን፥ አቤሮን፥ እና ኦን ከተባሉ ሦስት ሰዎች እና ከእስራኤል ልጆች ዝነኛ የሆኑ 250 አለቆች ወስደው በሙሴና በአሮን ላይ ተነሡ። ቆሬ የቡድኑ መሪ በመሆኑ ነው ሙሴ ለይቶ እርሱን የተናገረው። ይህ ዓመጽ ሲጠቀስ እርሱ የሚጠቀሰውም ስለዚህ ነው።

በሙሴና በአሮን ላይ ዓመጽን ያስነሣው ቆሬ የቆሬ ልጆች የተሰጣቸው አገልግሎት ቢኖርም በዚህ ያልረካና የአሮንን ልጆች የማጠን አገልግሎት ሊወስድ ቡድኑን የመራ ሰው ነው። የሮቤል ልጆች የዚህ ተባባሪ መሆናቸው ሮቤል የእስራኤል በኩር እንደመሆኑ እልቅናን ፈልገው ይመስላል። ዘኁ. 16፥13 ላይ ሙሴ ወደ እርሱ እንዲመጡ ሲልክባቸው፥ “በምድረ በዳ ትገድለን ዘንድ ወተትና ማር ከምታፈስሰው ምድር ያወጣኸን አይበቃህምን? ደግመህ በእኛ ላይ ራስህን አለቃ ታደርጋለህን?” ያሉት ይህንን ይገልጣል። እንጂ እነዚህም ቀድሞውኑ የወገናቸው የተመረጡ አለቆች ነበሩ፤ ዘኁ. 26፥9።

ጠቅላላው ምዕራፍ (ዘኁ. 16) ሲነበብ በፍጻሜያቸው ቆሬ ከዋናዎቹ ተባባሪዎቹ ከዳታንና ከአቤሮን እንዲሁም ከ250 ጭፍሮቹ ጋር አብሮ ምድር ተከፍታ የዋጠቻቸውና የጠፋ ሰው ነው። ይህ ሳያንስ በዚህ ቅጣት ተናድደው በማግስቱ በሙሴና አሮን ላይ የተነሡ የእስራኤል ልጆች ማኅበር ውስጥ በዚያ ቀን 14ሺህ ሰባት መቶ ተቀሰፉ።

ቆሬ ይህ ነው። ይሁዳ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ሲያስተምር ለምን ይህንን ሰው አብሮ ጠቀሰው? ቆሬ ተለክቶ፥ ተቆርሶ የተሰጠው የከበረ አገልግሎት ስላልበቃው ያልተሰጠውን ሊወስድ ሲዘረጋ በሌላው ሳይሆን በሰጪው ላይ መነሣቱን ያላስተዋለ ሰው ነው። የቆሬና የግብረ አበሮቹ ጥፋት የሙሴንና የአሮንን ሹመት አለመቀበል ነው። የዓመጻቸው መሠረትም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሥልጣንን መቃወም ነው። ሐሰተኛ ነቢያት ሥልጣን ያላቸውን እንደሚሳደቡ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ሙሴ በሕዝቡ ላይ መንፈሳዊ መሪ ብቻ ሳይሆን አስተዳደራዊ አለቃም እንደነበር ይታወቃል። ሆኖም ራሱን በራሱ የሾመ ሳይሆን የተጠራ የውክልና መሪና አለቃ ነው። ይሁዳ ይህን የጠቀሰው ሐሰተኛ ነቢያት በተለይ መንፈሳዊ ሥልጣንን፥ ማለትም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መቃወማቸውን ለማመልከት ይመስላል።

በዚህ የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣም የመቃወም ሂደት ውስጥ ዋና የጥቃት ትኩረታቸው ቤተ ክርስቲያን ናት። በቅርብ በቤተ ክርስቲያን 2ጢሞ. 2ን በተከታታይ ሳስተምር ቁ. 19 ያለውን ‘ሆኖም፦ ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል፥ ደግሞም፦ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል።’ ከሚለው የመሠረቱ ማኅተም የተባለውን ሐረግ ተመልክተን ነበር። ጥቅሱ ‘ሆኖም’ ብሎ መጀመሩ ከዚያ በፊት ከተናገረው ነገር ተነሥቶ ነው፥ ከዚያ ቀደም ሲል የጻፈው ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ነው። ስለ ከንቱ ለፍላፊዎች ስለ ሄሜኔዎስ እና ፊሊጦስ ከተናገረ በኋላ ነው ‘ሆኖም ያለው። ሆኖም ይህ መሠረት

ቆሞአል። በውስጡ የክብርና የውርደት ዕቃዎች ያሉበት ሕንጻ አለ፤ ሕንጻው መሠረት አለው። መሠረቱ ማኅተም አለው። መሠረቱ ላይ የተባለ፥ የተቀረጸ፥ የታተመ ነገር አለ። መሠረቱ አንድ ሆኖ ሁለት ነገሮች ናቸው የተጻፉት፤ 'ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል' እና፥ 'የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ' የሚሉ።

አንዱ ሐረግ እግዚአብሔርን የሚመለከት ሌላው ክርስቲያንን የተመለከተ ነው። ከሄሜኔዎስ እና ፊሊጦስ በኋላ ይህንን መናገሩ ከሐሰተኞች እና ከአስካጆች ጋር በማነጻጸር ነው። አንደኛው፥ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ያውቃል። እርሱ እግዚአብሔር ነውና ምንም የማያውቀው ነገር የለም። ሁሉን ያውቃል። የእርሱ የሆኑትን ደግሞ በእርግጥና አሳምሮ ያውቃል። በእግዚአብሔር እንደመታወቅ ልብን የሚያሳርፍ ሌላ እውነት ይኖር ይሆን? ሁለተኛው፥ የጌታን ስም የሚጠራ ደግሞ ከዓመጽ እንዲርቅ ተጠርቶአል። በዘኁ. 16 ያለው ታሪክ ሁለቱንም አሳቦች የሚያሳይ አንድ ታሪክ ነው። በተለይ ቁ. 5 የእርሱ የሆኑትን ማወቁንና ማሳወቁን፤ ቁ. 26-27 ደግሞ ከእነዚህ ሰዎች፥ ከድንኳናቸውና ከማደሪያቸው ዙሪያ መራቅን ይናገራል።

ሐሰተኛ ነቢያት እንዴት እንደሚጀምሩ ታሪካቸውን ከመሠረቱ ሄደን ስንመረምር የብዙዎቹ ጅማሬ ከቆሬና ከነአቤሮን ታሪክ ጋር ይመሳሰላል። ቤተ ክርስቲያን ያላትን ሥልጣን በመቃወም እና በማመጽ ነው የሚጀመረው። የነበሩባቸውን አብያተ ክርስቲያናት እንከናም የሚጀምሩትን እንከን አልባ አድርገው ባለ ራእይና መሥራች ተብለው አዲስ መሠረት ሲጥሉ፥ ከመሠረቱ ራሳቸውን መፈንቀላቸውን አያስተውሉም። የሐሰተኛ ሃይማኖቶችንና ማኅበሮችን ታሪኮች ስንመረምር ይህ እውነት ሆኖ እናገኘዋለን።

ሐሰተኞች ነቢያትና ቆሬ በዓመጽና በተሰጣቸው ክቡር ጸጋና የአካል ድርሻ ባለመርካት፥ ዓመጸኞችን በማስከተልና በማስነሣት ይመሳሰላሉ። ጥፋታቸውና ፍጻሜያቸውም ተመሳሳይ ነው።

ሠ. እድፈኞችና ነውረኞች፥ የራሳቸው እረኞች፥ ደረቅ ደመናና የተነቀሉ ዛፎች፥ የሚንከራተቱ ከዋክብት

12፥ እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ እንደ <u>እድፍ</u> ናቸው፤ እንደ <u>እረኞች</u> ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይጠብቃሉ፤ በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው

ደመናዎች፥ ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ ከነሥራቸው የተነቀሉ በቢጋ የደረቁ ዛፎች፥ 13፥ የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል፥ ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው።

በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ ይሁዳ የጠቀጠቃቸው የሐሰተኞች ነቢያትና አስተማሪዎች ባህርያት ብዙ ናቸው። በዚህ ክፍል ስድስት ነገሮች ተጠቅሰዋል። እያንዳንዱ ራሱ የቻሉ ትልልቅ ትምህርት ይወጣዋል። ግን በአጭር እንያቸው።

1. እድፍ ይላቸዋል። እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ እንደ እድፍ ናቸው። ንጽጽሩ ግልጽ ነው፤ የፍቅር ግብዣ ፍቅር እና ግብዣ፥ ደስታና ፍስሐ ያለበት ስፍራ ነው። የፍቅር ግብዣ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በየሳምንቱ በጌታ ቀን የጌታን ራት ካሰቡ በኋላ በንጹሕ ፍቅር የሚበሉት የምግብ ግብዣ ነው። በዚያ ስፍራ እድፍ መገኘቱ ያንን ንጹህ ኅብረት የሚበክል፥ የሚያቆሽሽ መሆኑን የሚያመለክት ነው። የእድፍ እድፍነት ጎልቶ የሚታየው ያለቦታው በንጹሕ ስፍራ ሲገኝ ነው። ይህ ቃል ይሁዳ ብቻ የጠቀሰው ቃል ነው። ይህ ቃል (σπιλάς - ስፒላስ) በቀጥታ ሲተረጎም ባህር ውስጥ የሚገኝ ጫፉ ብቻ የሚታይ ያገጠጠ ድንጋይ ማለት ነው። ቀራቢው ከሆነው ቃል (σπίλος - ስፒሎስ) ከሚለው ቃል ጋር ይቀራረባል። ይህኛው ነውር፥ እድፍ፥ እንከን ማለት ነው። በኤፌ. 5፥27 እና 2ጴጥ. 2፥13 ነውር እና ነውረኛ ተሰኝቶ ተጠቅሶአል። ሐሰተኞች በቅዱሳን ውስጥ ነውርና እድፍ ናቸው።

2. እንደ እረኞች ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይጠብቃሉ፤ ቃሉ በቀጥታ ሲተረጎም ያለ ፍርሃት ራሳቸውን ይመግባሉ፥ ይጠብቃሉ፥ ያሰማራሉ ነው። ልክ እረኛ መንጋውን ሊያበላ እንደሚመስግ እነዚህ መንጋውን ሳይሆን ራሳቸውን ያለ ፍርሃት፥ ያለ ኀፍረት፥ ያለ መሳቀቅ የሚመግቡ፥ የሚመስጉ ሰዎች ናቸው። የራሳቸው እረኛ ናቸው። ሐሰተኛ ነቢያት ዋና መታወቂያቸው መጋቢ ሳይሆኑ ተመጋቢ መሆናቸውና የማንም ተጠያቂ አለመሆናቸው ነው። ልክ በሕዝ. 34 እንደተጻፉት እረኞች ወይም ጌታ በዮሐ. 10 እንዳስተማረው እንደ ሞያተኛው እረኛ ያሉ ናቸው። እውነተኛ እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል እንጂ ራሱን አይጠብቅም። ሐሰተኞች ግን የራሳቸው ጠባቂዎች፥ መሳቢዎች፥ አጥጋቢዎች፥ ጠባቂዎች ናቸው።

3. በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው ደመናዎች፥ ደመናዎች ናቸው። ደመና ሁለት ጥቅም አለው። ጥላ ይሆናል። በሐሩር ጊዜ ደመና የሚናፍቁት ነገር ነው።ደግሞ ደመና ዝናብ ይቋጥራል። ደመና ካለ የመርጠብ፥ የመራስ፥ የመረስረስ፥ የመርካት ተስፋ አለ። እነዚህ ሰዎች ሁለቱም፥ ጥላውም እርጥበቱም የላቸውም። ጥላ እንዳይሆኑ በነፋስ የተወሰዱና የተበተኑ ናቸው። አሉ ሲባሉ የሉም። እነርሱን መከተል ራሱን ነፋስን እንደመለከት ነው። ዝናብ እንዳይጥሉና እንዳያረሰርሱ ደግሞ ውኃ የሌለባቸው

ናቸው። ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች የውሸት ተስፋ እንጂ የእውነት ጸጋ የላቸውም። ተስፋ የሚመስል ነገር አላቸው። ፈውሱ፥ ብልጽግናው፥ ሥልጣኑ፥ መጣሱ፥ ምኑቅጡ፤ አላቸው። ግን አይጨበጡም። በነፋስ የተወሰዱ የሚለው ቃል ነፋስ ተሸክሞ የሚያሽከረክራቸው የሚያዘዋውራቸው ማለት ነው። ውሸታም ተስፋቸው ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም የማይጨበጡ ናቸው። በስፍራቸው የሌሉ ብቻ ሳይሆኑ ስፍራም የሌእላቸው ናቸው።

4. ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ ከነሥራቸው የተነቀሉ በበጋ የደረቁ ዛፎች፥ ዛፎች ናቸው። ዛፍም እንደ ደመና ጥቅም አለው፤ ያስጠልላል፤ ጥላ ይሆናል፤ ፍሬም ይሰጣል። እነዚህ ዛፎች ግን አራት ነገሮች ሆነዋል፤ ፍሬ አያፈሩም።ደርቀዋል በበጋ (በበልግ)። ከነሥራቸው ተነቅለዋል። ሥራቸው በአፈር ውስጥ ቢቀር ኖሮ እንኳ ተስፋ ይኖራቸው ነበር። ሥራቸውም ተነቅሎአል። ሞተዋል፤ ያውም ሁለቴ ሞተዋል። መድረቃቸው መሞት ነው። መነቀላቸው የተረጋገጠ ሞታቸው ነው። ሐሰተኛ ነቢያት በድርቀት የተመቱ ፍሬቢስ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የፍሬ ብቻ ሳይሆን የመኖር ተስፋም የላቸውም።

5. የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር ማዕበል፥ ነውረኞች ናቸው። ነውራቸው ደግሞ ከውስጣቸው ነው የሚወጣው። ይህ አገላለጥ ባሕር ሲነዋወጥ ከባሕሩ ውስጥ ቆሻሻና ጉድፍ የሚወጣበትን መልክ የሚያሳይ አገላለጥ ነው። ልክ ኃይለኛ ማዕበል ከባሕር ውስጥ የሚደፍቅ አረፋውን እንደሚያወጣ እነዚህም ከውስጣቸው የገዛ ነውራቸውን፥ የራሳቸውን ነውር፥ አስነዋሪ፥ አሳፋሪ ሥራቸውን ያወጣሉ። አረፋው በባሕሩ ላይ እንደሚታይ ነውራቸውም ይታያል። ሐሰተኛ ነቢያት ነውረኞች ናቸው።

6. ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው። የሚንከራተቱ የሚለው ቃል ዘዋሪ ማለት ነው። ፕላኔት የሚለው ቃል የተሠራበት ነው። ቃሉ ማሳት ከሚለው ጋርም የተቆራኘ ነው። እነዚህ ከዋክብት መዞር ብቻ ሳይሆን መስመር የሳተ፥ ከምሕዋሩ የወጣ አሳች የሆነ አካሄድን የሚሄዱም ናቸው። ከዋክብትም ፕላኔቶችም ጨረቃዎቻቸውም ሁሉ በየዛቢያቸው ወይም እንዝርታቸው እየሾሩ ሌላ ትልቅ አካልን የሚዞሩበት ዐውድ አላቸው። እነዚህ ግን በምሕዋራቸው ሳይሆን ያለ ምሕዋራቸው የሚነጉዱ፥ የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው። ማረፊያ፥ ማደሪያ፥ መስመር፥ ትልም የሌላቸው ዘላኖች ናቸው።ተላትመው አደጋ ሊፈጥሩ ይችላሉ፤ ላይመለሱም ተወንጭፈው ይጠፋሉ። አካሄዳቸው ሁሉ ያለ መስመር፥ ያለ ሥርዓት ነው።

ሐሰተኛ ነቢያትም ልክ እንደዚህ ናቸው፤ መስመርና ሥርዓት የላቸውም፤ ወግና ስፍራ የላቸውም። እንደፈለጉ አዲስ መስመር እየነደፉ፥ አዲስ መንገድ እየቀየሱ፥አዲስ ትምህርት እየፈለሰፉ የሚጓዙ ዘላኖች ናቸው። ይሁዳ አካሄዳቸውን ብቻ ሳይሆን ፍጻሜያቸውንም ነው የሚናገረው። ልክ እነዚህ ከዋክብት ተንከራትተው ፍጻሜያቸው ከብርሃን ርቀው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንደሆነ ሁሉ የሐሰተኛ ነቢያት ፍጻሜም እንዲሁ ነው። 2ጴጥ. 2፥17ም ይህንኑ ይናገራል። ድቅድቅ ጨለማ ሐሰተኛ ነቢያት ከእግዚአብሔር ተለይተው ለዘላለም የሚቅቀጡበትን ስፍራ የሚያሳይ ነው።

ሐሰተኛ ነቢያት እንዲህ ናቸው። እድፎች፥ የራሳቸው መጋቢና ጠባቂ እረኞች፥ የተበተኑ ውኃቢስ ደመናዎች፥ ፍሬቢስ ንቃይና ደረቅ ዛፎች፥ ነውረኞች፥ ሲኖሩ ከመስመር የወጡ ተንከራታቾችና ፍጻሜያቸው ድቅድቅ ጨለማ የሆነ ናቸው። ከሐሰተኛ ነቢያት እና ከሐሰት አስተማሪዎች እንጠበቅ።

ረ. የፍርዳቸው ትንቢት፤ የሄኖክ ትንቢት

14-15፥ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ፦ እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭካና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።

16፥ እነዚህ እንደ ምኞታቸው እየሄዱ የሚያንጎራጉሩና ስለ ዕድላቸው የሚያጕረመርሙ ናቸው፥ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ አፋቸው ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል።

ይሁዳ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና የስሕተት አስተማሪዎች እየተናገረ አንድ የብሉይ ኪዳን ሰውን ምስክር አድርጎ ይጠቅሳል። በቁጥር 14-15 ስለ ሄኖክ ይናገራል። ይህ ሄኖክ በዘፍ. 5 እና ዕ. 11፥5 የተጻፈው ነው። በ1ዜና 1፥3 እና ሉቃ. 3፥37 በትውልድ ሐረጎች ውስጥም ተጠቅሶአል።

ይህ በዚህ ክፍል ሄኖክ እንደተናገረ የተባለው ቃል የሄኖክ ታሪክ በሚገኝበት በዘፍ. 5 አይገኝም። ነገር ግን መጽሐፈ ሄኖክ በተባለ የአጵቅሪፋ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። ይህ ማለት ታዲያ ከሄኖክ መጽሐፍ ውስጥ ይሁዳ ስለጠቀሰ መጽሐፈ ሄኖክ ወይም ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ መጽሐፎችን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቀኖና

የተገባቸው አያደርጋቸውም። ጳውሎስ ለምሳሌ፥ በሐዋ. 17፥28 እና ቲቶ 1፥12 ሌሎችን፥ ያውም ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከአይሁድ ጋር ምንም ቀረቤታ የሌላቸውን ሰዎች ጽሑፎች ወይም ንግርቶች ጠቅሶአል። ይህ አጠቃቀስ ለሰዎቹ ጽሑፎች እስትንፋስ መለኮትን በሙሉ ወይም በከፊል አያቀዳጃቸውም። ጠቃሹ የጠቀሰው ክፍል በጊዜው ያስተላለፈውን እውነት ለመግለጥ ግን አስተዋጽዖ አድርጎአል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የአጾቅሪፋ እና አዋልድ የሚባሉ ብዙ መጽሐፎች ይገኛሉ። ከእነዚህ መጽሐፎች አንዳንዱ ሃይማኖታዊ፥ ሌሎቹ ታሪካዊ፥ ሌሎቹ የቅኔና የምክር ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ውስጥ የመግባት ባህርይም ሆነ ብቃት ያልነበራቸው ስለሆኑ ራሳቸው አይሁድም እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አልተቀበሉአቸውም። ቤተ ክርስቲያንም አልተቀበለቻቸውም። ብዙዎቹ የተጻፉት እንዲያውም አዲስ ኪዳንም እንኳ ተጽፎ ከተጠናቀቀ በኋላ መሆኑ የታወቀ ሆኖአል። ከእነዚህ መጽሐፎች አንዳንዶቹ ቅይጦች ናቸው፤ አንዳንዶቹ ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር ይጣላሉ፤ አንዳንዶቹ በውስጣቸው ብዙ እውነቶችን የያዙ ናቸው። ሆኖም ያ ውብ ስነ ጽሑፍ ወይም ታሪካዊ ሰነድ ያደርጋቸዋል እንጂ ቃለ እግዚአብሔር አያደርጋቸውም።

ሄኖክ ከጥፋት ውኃ በፊት የኖረና ሞትን ሳያይ የተወሰደ ሰው ነው። ስለ ሄኖክ ዘፍ. 5፥24 እንዲህ ይላል፥ ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና። የሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ የሚያመለክተው አንጻራዊ ነገር አለ፤ ያም በጊዜው አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያላደረጉ ሰዎች መኖራቸውን ነው። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቆራኘ አካሄድ በቀጣዩ ምዕራፍ (ዘፍ. 6) የተጻፈው ነው።

ሄኖክ ከአዳም ሰባተኛ ሰው መሆኑን መጥቀሱ ያ ሄኖክ የኖኅ ቅድመ አያት የሆነው ሄኖክ መሆኑን ለመግለጥ እንጂ ሰባተኛ መሆኑ ምንም የተለየ ትርጉም ስላለው አይደለም። ሄኖክ በሚወለድበት ጊዜ አዳም ገና 622 ዓመቱ ነው። ወደ 300 ዓመታት አብረው ኖረዋል። የኖኅ አባቱና አያቱም (ላሜሕ እና ማቱሳላ) አዳምን ያውቁታል። ሄኖክ የኖኅ ቅድመ አያት ነው። እርሱ አካሄዱን ከአምላኩ ጋር አድርጎ ቢወሰድም ኃጢአተኞችን በኃጢአታቸው እንዲቀጣ፥ እንዲፈርድ እንደሚመጣ ትንቢትን ተናግሮ እንደነበር ነው ይሁዳ የጠቀሰው። ይህንን መጥቀሱ መልእክቱን አጠንክሮ ለማስተላለፍ ነው።

መልእክቱ ግልጽ የሆነ ነው፤ እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል የሚል ነው። ሄኖክ የተናገረው ያ ትንቢት በቀጣዩ፥ በልጁና በልጅ ልጁ

ትውልድ ፍጻሜ ላይ የሆነውን የጥፋት ውኃ የሚያመለክት፤ በድርብነትም መጪውን የፍጻሜ ፍርድ የሚያመለክትም ነው። በጥቅሱ ውስጥ ተደጋግሞ የተጻፈው ኃጢአት የሚለው ቃል የዓመጸኞቹን ድርጊት ብቻ ሳይሆን የድርጊቱን አመንጪ ልባቸውንም የሚያመለክት ነው።

የይሁዳ ነጥብም ይህ የኃጢአተኞች ዓመጽና የዚህ መዘዝ የሆነው የማይቀር ፍርድ እና ቅጣታቸው ነው። ኃጢአተኞችና ዓመጸኞች መቀጣታቸው የማይቀር ነው። ሐሰተኛ ነቢያት እና የስሕተት አስተማሪዎች የተሳካላቸው፥ የደረጁ፥ ባለ አዱኛ ቅንጦተኞች፥ ቱጃሮች፥ ዝነኞች፥ ሹመኞች፥ ቢመስሉም ወይም ቢሆኑም ያ ምኞት ቢበዛ ምድራዊ ዋጋቸው ነው። እውነተኛው ዳኛ የሰዎችን ድርጊት የሚበይን እውነተኛ ዳኛ ብቻ ሳይሆን ብቻ ሳይሆን የድርጊታቸውን ግፊትም የሚመዝነው ጻድቅ ፈራጅ ነው።

ቁ. 16፥ እነዚህ እንደ ምኞታቸው እየሄዱ የሚያንጎራጉሩና ስለ ዕድላቸው የሚያጒረመርሙ ናቸው፥ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ አፋቸው ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል።

ይህ ጥቅስ ስለ ሐሰተኞች ነቢያትና ስሑት አስተማሪዎች ባሕርያት ተጨማሪ ነጥቦችን ይዘረዝራል። በመጀመሪያ እንደ ምኞታቸው የሚሄዱ ናቸው። ምኞታቸው ደግሞ እደተጻፈበት ቃል አገላለጥ የገዛ ምኞታቸው፥ የራሳቸው ምኞት ነው። ፈቃዳቸውን በማንም እና በምንም ሳይሆን በምኞታቸው ነጂነት የሚያስጉዙ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ነው በሐሰተኛ ነቢያት ዘንድ ምንም ቁጥጥር የሌለበት፥ ምንም ተጠያቂነት የሌለበት የሥልጣንና የገንዘብ ባለቤትነት የሚታየው። ዳርና ድንበር፥ ሕግና ደንብ፥ ሥርዓትና መስመር የላቸውም። የተመኙትን ነገር ለማድረግ ምንም ዓይነት ተዐቅቦ የሚያደርግባቸውን ሰውም ሆነ ሥልጣን በቅርባቸው ማየት አይፈልጉም። የቡድን መሪነትን አጥብቀው ይጠላሉ፥ ያጥላላሉ። ምክር ከተሰጣቸው እንደ ምክር ሳይሆን እንደ ተመርጦ እንደሚጣል አስተያየት ብቻ ነው የሚያዩት፤ ካዩት ነው ያም። ለምኞታቸው ማስፈጸሚያ እንዲያውም የእግዚአብሔርን ቃልና ስምም የሚጠቅሱ አሉ። ለመባለግ፥ ንብረት ለመዝረፍ፥ ትዳርንና ውልን ለማስፈረስ፥ 'እግዚአብሔር እንዲህ ብሎኛል' እያሉ ለመናገርን የማይሳቀቁ ናቸው። ሐሰተኛ ነቢያትና የስሕተት አስተማሪዎች ገደብ እንደሌለው የገዛ ምኞታቸው የሚሄዱ ናቸው።

ሁለት ዓይነት መልክ ያላቸው ሰዎች ናቸው። አንጎራጓሪና ስለ ዕድላቸው አጒረምራሚዎች ናቸው። ማጒረምረምና ማንጎራጎር የሥጋዊነት፥ የአለመርካት፥ የአልጠግብ ባይነት ቀንደኛ ምልክት ነው። ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት ለእነዚህ ሰዎች ከኃጢአት እኩል ነው። ሰው በእግዚአብሔር ካልረካ በምንም ነገር መርካት እንደማይችል ከመጀመሪያ ረድፍ የሚቆጠሩ ሰዎች ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው። እነዚህ

ሁለት ቃላት በኖራቸው አለመርካትንና ጎዶሎን ማየትን ብቻ ሳይሆን ለሌላው በሆነው መቅናትንና አለመሳካትን የያዘ ነው። 'እድል' የሚለው ቃል የያዘው ያንን አሳብ ነው።

እንዲህ ውስጣቸው የተጨራመተ እፎይ ያላሉ ሰዎች ሆነው ደግሞ ከልክ ያለፉ፥ የተነፉ፥ ያበጡ፥ ታላላቅ ቃላት ይናገራሉ። ይህ ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል የሚለው ቃል እዚህና በ2ኤጥ. 2፥18 ብቻ የተጻፈ ነው። ሁለቱም ስለተመሳሳይ ሰዎች ነው የሚናገሩት። እነዚህ ሰዎች ቃላትን ይፈበርካሉ፤ ቃሎቻቸውን ትልልቅ ተስፋ ያዘሉ ያስመስሏቸዋል፤ በእግረ መንገድም የአላዋቂ አዋቂነታቸውንም ያስተዋውቁበታል።

ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ደግሞ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ ነው። ለሰው ፊት ማድላታቸው ከልክ ያለፈ ያበጠ፥ የተወጠረ ቃላቸውን ተግባራዊ አፈጻጸም የሚያሳይ ነው። ገንዘብ ካላቸው ሰዎች ገንዘባቸውን የሚያራግፉበት መንገዶች ብዙ ናቸው። የሚታዩ ሸቀጦችን በሐራጅ ከመሸጥ ውሸታም ተስፋን በገንዘብ እስከመሸጥ ድረስ ነው። በለስላሳ ቃላትም፥ በአዚምና በአፍዝ አደንግዝም ኪስና ቦርሳን፥ ካዝናንና የባንክ ደብተርን ሲያራቁቱ በስሌት ነው። እንዲረባቸው ማለት ለጥቅምና ለትርፍ ነው የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያደርጉት ማለት ነው። ሐሰተኛ ነቢያትና የስሕተት አስተማሪዎች ምንም ነገር ሲያደርጉ ጥቅማቸውን፥ ረባቸውን፥ ገቢያቸውን፥ ገበያቸውን አስልተው ነው። ለዘላለማዊው ቅጣትም ሆነ ሽልማት ዕውር እስኪሆኑ ድረስ በምድራዊ ረብ ዓይናቸውም ልቡናቸውም የታወሩ ሰዎች ናቸው።

ይሁዳ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና የሐሰት አስተማሪዎች ይህንን ካለ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል ወደ አማኞች ፊቱን መልሶ፥ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በማለት ምክሩን ይቀጥላል።

ምክር ለአማኞች

ሀ. ዘባቾች

17፥ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ፤

18፥ እነርሱ፦ በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባቾች ይሆናሉ ብለዋችኋልና።

19፥ እነዚህ የሚያለያዩ ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

ይሁዳ ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና የስሕተት አስተማሪዎች እየተናገረ እየተናገረ ቆይቶ ያንን ሳይተው ለቅዱሳን በቀጥታ ደግሞ ይናገራል። እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይላል። ከቁ. 5-16 ድረስ ያየነው ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ባህርያት የዘረዘረውን ነው። ከዚህም በኋላ የሚጨምራቸው ነገሮች አሉ፤ ግን ስለ እነርሱ ሲናገር ቆይቶ የመልእክቱ ተቀባዮች ለሆኑት ክርስቲያኖች ደግሞ የምክርን ቃል ይናገራል።

አሁን በቀጥታ በሁለተኛ መደብ እናንተ እያለ በቀጥታ ለእነርሱ ነው የሚናገረው። እስካሁንም ለእነርሱ ነው የተናገረው፤ ግን የነገራቸው ስለ አሳቻቹ ነው።ማስጠንቀቂያ ነው። አሁን ግን እነርሱን ነው የተናገረው። የተናገረው ፍሬ ነጥብም፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ፤ የሚል ነው። ሐሰተኞችን ለመለየትም፥ ከእነርሱ ለመጠበቅም ክርስቲያኖች ማድረግ ካለባቸው ዋና ዋና ነገሮች አንዱ አስቀድሞ ወደተሰጠው፥ ወደ ተነገረው እውነት፥ ወደ ቃሉ መመለስ ነው።

አዳዲስ ቃሎች በየጊዜው ሊመጡ ይችላሉ። ይመጣሉም። አዳዲስ ንግርቶች ሊነገሩ፥ ትንግርቶችም ሊታዩ ይችላሉ። አስቀድሞ የተሰጠውን፥ የተነገረውን ቃል ግን መጠምዘዝና መለወጥ የለባቸውም። የመለወጥና የመጠምዘዝ፥ መተካትም አቅም የላቸውም ማለት አይደለም። የሐሰተኛ ነቢያት ቃሎች ያኛውን እውነተኛውን ቃል የማያውቁትን ማታለልና እውነት መስሎ ማለፍ ይችላሉ። የሚያውቁት ግን አይታለሉም። ያንን ቃል ማሰብና ወደዚያ መመለስን ነው ይሁዳ የሚናገረው። እነዚህ ይሁዳ የጻፈላቸው ክርስቲያኖች ከጌታ በቀጥታ የሰሙት ሐዋርያት በዘመናቸውም ነበሩና እነርሱ የተናገሩትን ቃል ማሳሰቡ ነው። ሐዋርያት ሲል እነዚያን የክርስቶስን ሐዋርያት መናገሩ ነው። እነዚያ ሐዋርያት በእነዚህ ይሁዳ በሚጽፍላቸው ሰዎች ዘንድ የታወቁና ከጌታ የተማሩትን ያገለገሉ ናቸው። ይታወቃሉ። እነዚህ ሐዋርያት እነማን እና የትና መቼ እንደተናገሯቸው በዝርዝር አናገኝም። ግን ማስጠንቀቂያዎቹ በአዲስ ኪዳን ገጾች ተጽፈውልናል፤ ለምሳሌ፥ ሐዋ. 20፥29፤ 1ጢሞ. 4 እና 6፤ 2ጢሞ. 3፤ ቲቶ 1፤ 2ጴጥ. 2፤ 1ዮሐ. 2 እና 4፤ ወዘተ።

ሐዋርያት ነን የሚሉ ሰዎች በዘመናችን በካርቦን ኮፒ እየተባዙ ስለሆነ ይህ ቃል እነዚህን ሐዋርያት ወይም እነርሱን የሚመስሉትን መናገሩ ከቶም አይምሰለን። አሳቡ ያተኮረው እንዲያውም ሐዋርያቱ ላይ ሳይሆን ቃሉ ላይ ነው። አስቡ የተባሉት የተናገሩትን ሐዋርያቱን ሳይሆን ሐዋርያቱ የተናገሩትን ቃል ነው፤ ‘ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ’ ነው። ዛሬ ይህ ቀድሞ የተነገረው ቃል ተጽፎ የተላለፈልን ቃል ነው። ከሐሰተኛ ነቢያት፥ ከሐሰት አስተማሪዎች፥ ከስሕተት አለማማጆች ለመጥበቅ እኛም

ማድረግ ያለብን ይህንን አንድ ነገር ማድረግ ነው፤ ቀድሞ የተነገረውን ቃል ማሰብ። ቀድሞ የተነገረውን፥ የተጻፈውን ቃል የሚያስተውሉ ሰዎች በሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ድንገተኛ የጥቃት ወረራ ሊይካሄድባቸውም። በተጠንቃቂዎች ዘንድ ያልታሰበ፥ ያልተጠበቀ ወረራ ብሎ ነገር የለም። ወረራው ሊኖር ይችላል፤ ጥቃትና ሰለባነት ግን የለም። ዛሬ ያለነው ክርስቲያኖች ይሁዳ እንደጻፈላቸው እንደነዚያ እኛም ማድረግ ያለብን ቀድሞ የተነገረውን፥ የተጻፈልንን ቃል ማሰብ ነው።

ይሁዳ ድርብ ምስክሮችን እየጠራ መሆኑን እናስተውል። አስቀድሞ ከቀደሙቱ ሔኖክን እንደ ምስክር ጠቀሰ። ይህንን ቀደም ባለው በክፍል 13 (ይሁ. 14-16ን ስናይ) ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ከራሳቸው ዘመን ሐዋርያት ነው ምስክር የሚጠራው። ሐዋርያቱ ስለ እነዚህ ሰዎች የተናገሩት፥ እነዚህ ሐዋርያት የነገሯቸው አሳቹቹ 'በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባኞች ይሆናሉ፤ የሚያለያዩ ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው' ብለው ነው።

ይሁዳ ሐዋርያቱ ስለተናገሩባቸው ስለ እነዚህ ሰዎች ባህርያት ከመናገሩ አስቀድሞ ስለ ዘመኑ ተናግሮአል፤ በመጨረሻው ዘመን ብሎ። ያ ያኔ በመጨረሻው ዘመን የተባለው እስካሁድ ድረስም ያለው ከጌታ መምጣት በፊት ያለው ዘመን ነው። ከያኔ ይልቅ አሁን በጣም ወደ ጌታ መምጣት የቀረብን መሆናችን እነዚህ ነገሮች በይበልጥ እንድናይ አድርጎናል።

ቁ. 18 በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባኞች ይሆናሉ ይላል። የዐረፍተ ነገሩ ተሳቢ ቃል ሰዎቹ ዘባኞች መሆናቸው ነው። ዘባኞች የሚሆኑት ደግሞ በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው በመሄድ ነው። ይህ ዘባኞች የሚለው ቃል እዚህ እና 2ጴጥ. 3፥3 ይገኛል። ግሱ በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥም መሳለቅ፥ መዘባበት፥ መዘበት እየተባለ ተጠቅሶአል፤ ለምሳሌ፥ ማቴ. 2፥16፤ 27፥29-31፤ ሉቃ. 14፥29-30፤ ወዘተ። ዘባኞች ተሳላቂዎች፥ ፌዘኞችና አፊያዦች፥ ቀላጆችና ቀላማጆች፥ አቅላዮችና ሌላውን በማጣጣል መሳቂያና የተናቀ አድራጊዎች ናቸው። ዘባኞች ተግባራዊ ናቂዎች ናቸው።

ሐሰተኛ ነቢያት ዘባችነታቸው በንቀታቸው ይታያል። እግዚአብሔርን ይንቃሉ፤ ሰዎችንም ይንቃሉ። ሲያውቋቸውና ሲነቁባቸው ስልታቸውን ይቀይራሉ። እስከዚያ ግን የሚከተሏቸው ሰዎች በጥቅሉ የሳቱላቸውና ያላወቋቸው ሞኞች ስለሆኑ በእነዚህ ላይ ሲሰለጥኑባቸው በዘባችነትና በፌዝ ነው። በአፍሪቃ ሐሰተኛ ነቢያት ሰዎችን ከጉባኤ ወደ መድረክ አውጥተው እንደበቅሎ ሲጋልቧቸው፥ በወለል ላይ አጋድመው ሲረማመዱባቸው መታየት የተለመደ ሆኖአል። በሰዎቹ ላይ በተግባር ይዘብታሉ።

እግዚአብሔርም ወዲያው እጅ በእጅ ከፍሎ ስላልቀጣቸው በእርሱም ይዘብታሉ። ቃሉን እያወላገዱና እየጠመዘዙ በቃሉም ይዘብታሉ። ዘባኞች ናቸው።

ዘባችነታቸው በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው በመሄድ ነው። ቀደም ሲል በቁ. 4 እነዚህ ሰዎች በኃጢአተኝነት የሚላለሱ መሆናቸውን ተመልክተናል። እዚህን ያ አሳብ ነው የተደገመው። ቀደም ሲል ይሁዳ የጻፈውን ሐዋርያቱ የነገሯቸውን ያንን ነው እዚህም የደገመው። በኃጢአተኝነት መሄድ፥ መጓዝ የሐሰተኛ ነቢያትና የሐሰት አስተማሪዎች መለያ ምልክት ነው። የሐሰተኛ ነቢያት በኃጢአት መሄድ ድፍረት የተሞላበትና አንዳንዴም ለኃጢአታቸው መንፈሳዊነታቸውንና ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ የሚፈጽሙት መሆናቸውም ነው።

በኃጢአተኝነት የሚሄዱት ደግሞ እንደ ገዛ ምኞታቸው ነው። ይህ እንደ ገዛ ምኞታቸው የሚለው ሐረግ የተጻፈበት የመጀመሪያው ቃል፥ እንደ ራሳቸው ከቅድስና የራቀ፥ መንፈሳዊነትና ክቡርነት የሌለበት ፍላጎትና ምኞት ያሰኘዋል። ሕያው ቃል እና መደበኛ ትርጉም፤ ርኩስ የሆነውን ምኞታቸውን የሚፈጽሙ ዘባኞች ያሰኘዋል። ርኩስ ምኞት የሚለው አሳብ በመጀመሪያው ቋንቋ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል። ምኞት ወይም ፍላጎት በራሱ ክፉ አይደለም። ጤናማ ምኞት አለ። ይህኛው ምኞት ጤናማ አለመሆኑን ለማሳሰብ ነው የገዛ ምኞት፥ እና ቅድስና የጎደለው ምኞት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ምኞት ነው። በቁ. 16 እንደምኞታቸው የሚሄዱ፥ ምኞታቸው የሚነዳቸው፥ ለፍላጎታቸው ምንም ተዓቅቦ የሌላቸው ሰዎች መሆናቸውንም ተመልክተናል።

ሐሰተኛ ነቢያት እና የሐሰት አስተማሪዎች ምድራዊውን፥ ሥጋዊውን፥ ዓለማዊውን፥ ሥልጣናዊውን፥ ገንዘባዊውን ምኞት ሲመኙ ለምኞታቸው ዳርቻ የለውም። በቃኝን አያውቁም። የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለት ነውር ብቻ ሳይሆን ኃጢአት ይመስላቸዋል። ገንዘብን የሚሰበስቡባቸውን ስልቶች ስናጤን እንደ አልቅት በቃኝን የማያውቁ መሆናቸውን ማየት አይሳነንም። ሥልጣናቸውን ለመጠበቅ የሚሄዱበትን አካሄድ ስናይ ጨካኞች መሆናቸውን ማየት አያቅተንም። ቅድስና የሌለበትን ርኩስ ምኞታቸውን ለማሳካት በምንም ነገር ላይ ይረማመዳሉ።

ይሁዳ ስለ እነዚህ ሰዎች የተናገረው የመጨረሻው ነገር፥ የሚያለያዩ ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው' ይላቸዋል። የሚለያዩት ቅዱሳንን ነው። መለያ መሳሪያቸውም የሐሰት ትንቢትና ትምህርታቸው ነው። ሐሰተኞች ነቢያትና አስተማሪዎች ሰዎችን ወንጌል በመስበክ አይደለም ማኅበራቸውን የሚጀምሩት፤ ወንጌል የላቸውም። በመለየት፥ በመነጠል፥ በመክፈል፥ በመንፈቅ ነው የሚጀምሩት። ኑፋቄ ማለት ይህ ነው።

እነዚህ ሰዎች ሥጋውያን እና መንፈስ የሌላቸው ናቸው። ሥጋውያን የሚለው ቃል እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚመላለሱ ደመ ነፍሳውያን ናቸው። ቃሉ ራሱ ያንን ነው የሚላቸው። ደመ ነፍሳውያን እንደ እንስሳት ማንነታቸውን ተፈጥሮ የሚነዳቸው የሆኑ ሰዎች ናቸው። ከላይ እንዳየነው ምድራዊ፥ ሥጋዊ፥ ዓለማዊ ፍላጎትና አምሮት የሚገዛቸው ሰዎች ናቸው። መንፈስ የሌላቸው ሰዎች ናቸው፤ መንፈስ ቅዱስ ያልገዛቸው ብቻ ሳይሆኑ የማይኖርባቸውም ናቸው። የዚህ ምስክሩ ኑሮአቸው፥ አካሄዳቸው ነው። በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ነው የተባልነው። የሚሄዱበት አካሄዳቸው እንዲህ ነው።

ይሁዳ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ በማለት በቁ. 17 የጀመረውን አሳብ በቁጥር 20 ላይም፥ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በማለት ይቀጥላል። ጌታ ቢፈቅድና ብንኖር በቀጣዩ ጥናት እናየዋለን።

ለ. እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ

20፥ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ፥

21፥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።

22፥ አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፥ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥

23፥ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።

በቁጥር 20 ላይ እንደገና፥ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ ይላል። ይህም በቁጥር 17 የጀመረውን አሳብ እንደገና ማጠንከሩ ነው። በመካከልም በቁ 18-19 ስለ ሐሰተኞች መናገሩ ሁለቱም ወዳጆች ያላቸው እና ዘባኞች ያላቸው በንጽጽር እንዲስተያዩ ነው። እነዚህ ይህ መልእክት የተጻፈላቸው ‘ወዳጆች’ የተባሉት ቅዱሳን እዚህ ትጋታቸውን ጠቅሶአል። ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ ይላል። ይህ የተቀደሰ ሃይማኖት ቀደም ሲል በቁጥር 3 ያየነው ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠው እምነት ነው። እዚያ እንደተመለከትነው ይህ እምነት ለአንዴና ለመጨረሻ የተሰጠ፥ ተደጋግሞ የማይሰጥ፥ ደጋግመው የማይቀበሉት፥ የማይሻሻል፥

እያረጀ የማይታደስ፥ አዳዲስ ነገሮችና ቅጥያዎች በላዩ የማይቀጠሉበት ሃይማኖት ወይም እምነት ነው።

ይሁዳ እዚህ የሚለው ይህ አስቀድሞ የተቀበሉት አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተሰጠ ሃይማኖት ይዘውት የሚቀመጡት ሳይሆን የሚታነጹበት፥ የሚገነብቡበት እምነት ነው። ክርስትና የጎበረት ሃይማኖት እንደሆነ ሁሉ የግል እምነትም ነው። ቀደም ሲል በቁጥር 3 ጠቅልሎ ያቀረበውን ሃይማኖት እዚህ ተሳቢ አድርጎ የእናንተ ሃይማኖት፥ ሃይማኖታችሁ ይለዋል። የተቀደሰም ይለዋል። ይህ የተቀደሰ የሚለው እስካሁን ሲዘረዘር ከቆየው የሐሰተኛ ነቢያት እና የሐሰት አስተማሪዎች ሐሰተኛ ሃይማኖትና አካሄድ ፈጽሞ የተለየና የራቀ ባህርይ ነው። ሃይማኖቱ የተቀደሰ መሆኑን ለመግለጥ የተጠቀመው ትልቅ አበላላጭ ቃል ነው። ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ነው ያለው። ይሁዳ እጅግ የተቀደሰ የመሆኑን አመልካች ቃል መጠቀሙ ልዩነታቸውን ይበልጥ ለማሳየት ይመስላል። ይህ እጅግ የተቀደሰው የተቀባዮቹ እምነት ምን መሆኑን በመልእክቱ መግቢያ ላይ በአብ ከመወደዳቸውና ለኢየሱስ ተጠብቀው ከመጠራታቸው ጋር አያይዞ ተናግሮታል። እነዚህ በክርስቶስ ያመኑ በደሙም የነጹ ቅዱሳን ናቸው። ይህ ነው የተቀደሰ ሃይማኖት።

ይህ የተቀደሰ ሃይማኖት ራስን የሚያንጽም ወይም ራስ የሚታነጽበትም ነው። ስለዚህ ነው ይሁዳ በዚህ እምነት ወይም ሃይማኖት ራሳቸውን ለማነጽ እንዲተጉ ያሳሰበው። ቅዱሳን በጎበረት እንደሚታነጹ ሁሉ በግል ደግሞ ራሳቸውን ለማነጽ ይተጋሉ። በዚህ እምነት ውስጥ መገኘት ትልቅ ጥሪ፥ የከበረ ግንኙነትም ነውና በውስጡ መገኘቱ ብቻውን ሕይወትን የሚያንጽ፥ የሚገነባ ጉልበት አለው። ያንጻል። ይህ ይሁዳ እዚህ የጠቀሰው የሃይማኖት ትጋት ከስፍራችን የተነሣ የሚኖረንን ሥራችንን ያሳያል። ስፍራ ሥራን ይይዛል። ስፍራ ሥራን ያሳያል።

አምኖ መወዘፍ ሊያንጽም፤ ሊይገነባም። እምነት ትጋትን ይጠይቃል። ጥረትን ይጠይቃል። ለመዳን ምንም ጥረት አንጠየቅም። የተፈጸመውን ከመቀበል በቀር። ሆኖም ዕድገትና ጥንካሬ ልፋትና ጥረት ይጠይቃል። ይህ ትጋት እዚህ ይሁዳ አጠንክሮ ከተናገረው ከሐሰተኞች ከመጥጠበቅ ጋር የተቆራኘም ነው። የታነጸና የተገነባ ክርስቲያን በስሕተት ትምህርት አሳችነትና በሐሰተኛ ነቢያት ከንቱ ድለላ አይወሰድም። ራሱን የሚያንጽ፥ የሚገነባ፥ የሚያሳድግ ክርስቲያን በሚመጣው የትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገመ፥ እየወደቀ፥ እየተሰናከለ፥ እየተደፋ፥ እየተነሣ አይጓዝም።

ትጋት ከውስጥ፥ ከፍላጎት የሚመነጭ አለመታከትና የመቀጠል አካሄድ ነው። የሚያድጉ ክርስቲያኖች የሚተጉ ክርስቲያኖች ናቸው። መንፈሳዊ እድገት ኃላፊነት

አለበት። እድገት ምትሓታዊ አይደለም። እንደ ዮናስ ቅል በአንድ ሌሊት አድጎ አይታደርም። እድገት ትጋትን፥ ልፋትን ይጠይቃል። መንፈሳዊ እድገታቸውን በሌላ ሰው እጅ ላይ የሚያስቀምጡ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላይ ትልቅ ጥፋት የሚፈጽሙ ሰዎች ናቸው። አንዳንድ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ምግባቸውን ሌሎች እንዲያዘጋጁላቸው ብቻ ሳይሆን አቅርበው እንዲያበሷቸውም፥ እንዲያኝርሷቸውም ራሳቸውን ያሰነፉ ሰዎች ናቸው። ሁሌ ሌሎች እንዲያስተምሯቸው ራሳቸውን የወዘፉ ናቸው። የሚቀጥለው ሐረግ እንደሚያሳየው ሌሎች እንዲጸልዩላቸውም ራሳቸውን ያሰነፉ ናቸው።

ራስን ከማነጽ ጋር ተቆራኝቶ የተጠቀሰውና የትጋት አንዱ ገጽታ የሆነው ጸሎት ነው። በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ይላል። በተቀደሰ ሃይማኖት መታነጽ ከጸሎት ተለይቶ መከናወን አይችልም። ራሱን የሚያንጽ ክርስቲያን ሌሎች እየጸለዩለት በጸሎት ምጽዋት የሚተዳደር ሰው አይደለም። በጸሎት የሚተጋ እንጂ። ሃይማኖት በተፈጥሮው የአምላክና የአምላኪ የግንኙነት መንገድ ነው። ተመላኪና አምላኪ የሚገናኙበት ዋነኛው የግንኙነት መስመር ጸሎት ነው። ጸሎት ደግሞ ጸሎትነቱ፥ ግንኙነቱ በመንፈስ ሲታገዝ፥ በመንፈስ ቅዱስ ረጂነት ሲሆን ነው። ሮሜ. 8፥26-27 ይህን ድንቅ እውነት ይነግረናል። ኤፌ. 6፥18ም በመንፈስ ጸልዩ ይላል። ክርስቲያንን ለጸሎት የሚያነሣሳም የሚያተጋም መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ባነሣሳ ቁጥርም፥ ባበረታ ልክም የመጸለይን አስፈላጊነት መረዳት ተገቢ ነው። ጸሎት ግንኙነት እንጂ ሥርዓት አይደለም። ጊዜና ቦታ አይወሰንለትም፤ ሁኔታዎችም አይገድቡትም። በመንፈስ መጸለይ ከሐሰተኛ አስተማሪዎችና ከሐሰተኛ ነቢያት መከላከያ ብቻ ሳይሆን ራስን የማነጽ የአሸናፊነት ምስጢርም ነው። ጸሎት በተቀደሰ ሃይማኖት ውስጥ የመቆየት የቅድስና ሕይወት ምስጢር ነው።

የቁጥር 20 እና 21 ዋናው ግስ ‘ጠብቁ’ የሚለው ነው። የቀሩት ግሶች ወደዋናው አመልካቾች ናቸው። እየተጋችሁ፥ እየጸለያችሁ፥ እየተጠባበቃችሁ ጠብቁ። ምን ጠብቁ? ራሳችሁን ጠብቁ። በምን ጠብቁ? በእግዚአብሔር ፍቅር ወይም በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ጠብቁ። ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ። የጌታ ምሕረት ወደ ዘላለም ሕይወት ስንገባ የተቀበልነውም፥ አሁን የምንኖርበትም፥ ሲመጣና ፍጹማን እስኪደርገን የምንጠባበቀው ምሕረትም ነው።

የእግዚአብሔር ፍቅር የአማኞች ትክክለኛ አድራሻ ነው። በተለይ ሐሰተኛ ነቢያት እና የስሕተት ትምህርቶች ሰዎችን በሚያዋክቡበት ጊዜ፥ ሰዎች በሐሰት ትንቢቶች እየዋዠቁ ስፍራቸው በሚጠፋባቸው ጊዜ፥ እግዚአብሔርን ከሁኔታዎችና ከገጠማቸው ነገሮች ብቻ አንጻር በሚያዩበትና በሚለኩበት ጊዜ፥ በፍቅሩ ውስጥ መገኘት አለመጥፋትን ብቻ ሳይሆን አለመናወጥንም ይፈጥራል። የእግዚአብሔር ፍቅር

ተለዋዋጭ አይደለም። ከፍቅሩ የሚለየን ምንም ነገር የለም። አስቀድሞ የወደደንም ገና ጠላቶች ሳለን ነው። በዚህ ፍቅር ውስጥ ረክቶ መቀመጥ ተጠራጥረነው በሐሰተኞች እንድንካለብ ያደርገናል። በስሕተት ሽንገላቸው እንዳንወሰድ ያደርገናል።

ቁጥር 22 እና 23 የስሕተት አስተማሪዎችን እና በእነርሱ ተጽዕኖ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን እንዴት መቅረብ እንዳለብን ያሳያሉ። ቁጥር 22፥ አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ ይላል። ይህኛው የቃሉ አተረጓጎም ከብዙ ትርጉሞች ለየት ስለሚል በተለያዩ ትርጉሞች እንየውና ወደ አሳቡ እንመለስ።

- አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ። 1954 (ቀኃሥ)
- ተጠራጣሪ ለሆኑት ራሩላቸው። (መደበኛ)
- ለሚጠራጠሩትም ርኅራኄንና ምህረትን አሳዩዋቸው። (ሕያው ቃል)
- ለሚጠራጠሩ ሰዎች ርኅራኄ አድርጉላቸው። አዲስ ትርጉም (ቀባአ)
- እኩሉንም ማሩ ስትለያዩ። (አባ ሮሜ)

የተጻፈበት ቋንቋ καὶ οὓς μὲν ἐλεεῖτε διακρινόμενοι, ይላል። የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ቃላት በበኵረ ጽሑፉት ትንንሽ የፊደላት መለያየቶች ቢኖሩባቸውም (የተለወጡት ቃላት ελεατε / ελεειτε እና διακρινομενοι / διακρινομενους ናቸው።) ይህ ትርጉማቸውን አይለውጠውም።

ከአባ ሮሜ ትርጉም በቀር በቀሩት ሁሉ ተከራካሪዎች እና ተጠራጣሪዎት የሚለው አሳብ ገብቶአል። አመልካችነቱም ምሕረት የሚደረግላቸውን ሰዎች ሆኖ ባህርያቸውን የሚያመለክት ይመስላል። ትርጉሙ ግን ወደ አባ ሮሜ የሚቀርብ ነው። እንዲሁም (ደግሞም) አንዳንዶችን ማሩ መርምራችሁ (ለይታችሁ፥ ፈትሻችሁ) የሚል ነው።

በዚህ በምጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱስ (የ1954 ትርጉም) ይህ መከራከር የተሰኘው ግስ (διακρίνω) በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ቃላት ተገልጦአል። በማቴ. 16፥3፤ ሐዋ. 15፥9፤ 1ቆሮ. 11፥29፤ 14፥29 መለየት ተብሎአል። በማቴ. 21፥21፤ ማር. 11፥23፤ ሐዋ. 10፥20፤ 11፥12፤ ሮሜ 4፥20፤ 14፥23፤ ያዕ. 1፥6፤ መጠራጠር ተብሎአል። በ1ቆሮ. 4፥7 መበለጥ (የተለዩ መሆን)፤ በ1ቆሮ. 6፥5 ማስተዋል (መፍረድ)፤ በ1ቆሮ. 11፥31 መመርመር፤ በያዕ. 2፥4 ክፉ አሳብ (ማዳላት)፤ በሐዋ. 11፥2፤ ይሁ. 9 እና 22 መከራከር ተብሎአል።

በ1954 ትርጉም በይሁዳ መልእክት ውስጥ በሁለቱም ጥቅሶች (ቁ. 9 እና 22) መከራከር ተብሎአል። ምናልባት ከሐሰት አስተማሪዎችና ሐሰተኛ ነቢያት ጋር ስለተቆራኘ ክርክር፥ በቃላት መዋጋትና ንትርክ እንደሚኖር ታሳቢ ሆኖ ይሆናል። ነጥቡ ግን አንዳንዶችን፥ ፈትሻቸሁ፥ መርምራችሁ፥ ማንነታቸውን ለይታችሁ ራሩላቸው ነው። ይህ ጅምላ ርኅራኄ ሳይሆን ማንነትን አውቆ መራራት ነው። ሐሰተኛ ነቢያት አሳቾች የመሆናቸውን ያህል ሳቾች ወይም ስለባዎችም ናቸው። ስለዚህ ተለይተው በእርግጥ ከመታወቅ ጋር ርኅራኄ፥ ኀዘኔታም ያሻቸዋል። የሚመለሱ ከሆኑ ይህ ዕድል ይሰጣቸዋል።

አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥ እነዚህ ሰዎች ለፍርድ የተጻፉ መሆናቸውን አስቀድመን ተመልክተናል። እሳት የሚጠብቃቸውን ፍርድ የሚያመለክት ገላጭ ቃል ነው። እነዚህን ሰዎች ከስሕተታቸው መመለስ በእርግጥ እነርሱን ብቻ ሳይሆን እነዚህ ሰዎች ይዘዋቸው የሚነጉዱትንም፥ ቢያንስ ወደፊት ሊያስቷቸው የሚችሉትን ሰዎች ማትረፍ ነው። ይህ ጥቅስ የሚያሳየን ምንም አንኳ ለፍርድ የተጻፉ ቢኖሩም ከእነዚህ ኀራ የሚተርፉ መኖራቸውንና ለእነዚህ መዝዘርጋት ትርፍ እንዳለውም ነው። ይህ መንጠቅ ትግልን፥ ተጋድሎን፥ ወረራን፥ በጉልበት መውሰድን የሚያሳይ ነው። ዋጋ የሚጠይቅ ገድል ነው።

እነዚህን ሰዎች ለመመለስ የሚደረገው ተጋድሎ ሥራቸውን ብቻ ሳይሆን ሥጋቸውን የነካውን ልብስም በመጥላትና በመጸየፍ እነርሱን ግን በፍርሃት ማዳን ነው። እንዳለፈው ጥቅስ እዚህም ላይ የአማርኛው ትርጉም ለየት ያለ አተረጓጎምን ተከትሎአል። የአባ ሮሜን ትርጉም ልውሰድና እንዲህ ይላል፤ “እኩሉን ግን በፍርሃት አድንዋቸው ከእሳት ነበልባልም ስትነጥቋቸው፤ ደግሞም ከሥጋ የረከሰችውን ልብስ ስትጠሉ።” ቃሉ በእርግጥም መማር ሳይሆን ማዳን፥ መታደግ፥ መናጠቅ ነው። ይህ የታዳጊነት ወይም የተናጣቂነት ሥራ ፍርሃት ከሌለበት የእሻል ባይነት፥ የኩራትና የትምክህተኛነት ሥራ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ፍርሃትና ምሕረትም አብረው ተቋጥረው ተያይዘዋል። የዚህ ክፍል የመጨረሻው ጥቅስ ያንን ያሳስባል።

ቁ. 23፥ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ። ይላል። ቀደም ሲል ያየነው መማር ወይም ርኅራኄ ማሳየት በስሕተት ውስጥ የመታሰራቸው አሳዛኝ ሁኔታ ርኅራኄን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። ሐሰተኛ ነቢያት እና የሐሰት አስተማሪዎች ዘንድ ዘንድ ብዙ የሚያረክሱ ነገሮች ይገኛሉ። ቀደም ሲልም ጥቂቶቹን ይሁዳም ዘርዝሮአቸዋል። ሐሳውያን ነቢያትና አስተማሪዎች ትምህርታቸው ያረከሳል፤ ዓላማቸውና ግባቸው የእግዚአብሔር ክብር ስለሌለበት ርኩሰት ነው፤ ምኞታቸው ርኩስ ነው። ማንነታቸውን የከደነው ልብሳቸውም እንኳ የረከሰ ልብስ መሆኑ የኃጢአታቸውን መግነን የሚያሳይ ስዕላዊ ምሳሌ ነው።

ሰውን የሚያረክሰው ከውስጥ የሚወጣው እንደሆነ ጌታ አስተምሮአል፤ ማር. 7፥21-23። ይሁዳ ከእነዚህ ሰዎች ከውስጣቸው የወጣው ቀርቶ ከውጪ የነካቸውም እንኳ የተጠላ መሆን አለበት ሲል ምን ያህል ፍጹም የሆነ ርኩሰት እንዳለበት ያመለክታል። ሥጋቸው ያረከሰውን ልብስ መንካት እንኳ የተጠየፈ መሆኑ በሐጌ 2፥11-14 ያለውን ምሳሌ ያሳስባል። ርኩሰት ያረከሳል፤ የሐሰተኛ ነቢያት እና የሐሰት ትምህርት ርኩሰት በቀላሉ ሊገባ ይችላል፤ በቀላሉ ግን አይወጣም፤ ስለዚህ ትልቅ ጥንቃቄ የተገባው ነው። ለዚህ ነው እነዚህን ሰዎች ማዳን ወይም መታደግና ፍርሃት ደግሞ አብረው መቆራኘታቸው። ይህ ፍርሃት ወጥመድ ከሆነው ኃጢአታቸው ጠላፊነት ራስን መጠበቅን የሚያሳስብ ነው።

ቡራኬ

24፥ ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው፥

25፥ ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን።

ይሁዳ አጭር መልእክቱን የደመደመው በቡራኬ ቃል ነው። ቡራኬው እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት የሚያደርገውን በመግለጥ ይህን እግዚአብሔርን በማክበርና ከፍ በማድረግ ነው።

በመልእክቱ ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎችን በግልጽ አስቀምጦአል። በአንድ ወገን የሳቱትና አሳቾቹ፥ ከሐዲዎቹና ፍርደኞቹ የጠፉት ሰዎች ሲሆኑ በሌላ ወገን ደግሞ ወዳጆች እያለ የሚጠራቸውና ይህንን መልእክት የጻፈላቸው የዳኑት ሰዎች ናቸው። መዳናችን የእውነት መዳን ከሆነ፥ በእውነት ከጌታ ጋር ግንኙነት መሥርተን እርሱን ጌታችን አድርገነው ከሆነ እርሱ ሊጠብቀንና ሊያቆመን፥ እስከ ፍጻሜ ሊያጸናን፥ በእርሱ ብንኖር በእኛ ሊኖር፥ ከእጁ ማንም ላይወስደን፥ ተስፋና ዋስትና ሰጥቶናል። ችሎታም አለው።

የቡራኬው ባለቤት በቁ. 25 ያል የተጻፈው ብቻውን የሆነው አምላክና መድኃኒታችን ሲሆን በቁ. 24 አማኞቹን በተመለከተ አድራጎቱ በሁለት ጠንካራ ግሶች ተጽፎአል። እንዲጠብቃችሁ እና እንዲያቆማችሁ።

ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ። ይህ አለመሰናከል የሚለው ቃል በይሁዳ ብቻ የተጠቀሰ ቃል ነው። ስሩ የሆነውን መሰናከል የሚለውን ቃል ከይሁዳ ሌላ ጳውሎስ (ሮሜ 11፥11)፤ ያዕቆብ (ያዕ. 2፥10 እና 3፥2)፤ እንዲሁም ጴጥሮስ (2ጴጥ. 1፥10) ተጠቅመውታል። መሰናከል ከመውደቅ በፊት ያለ ሁኔታ ነው።

በጉዞ ውስጥ እንቅፋት አለ፤ ትብታብ አለ። እንቅፋት ያደናቅፋል፤ ትብታብ ያሰናክላል። አንድ ሰው እንቅፋት ቢመታው፥ መሰናከል ቢያሰናክለው፥ ትብታብ ቢጠልፈው፥ መጀመሪያ ይፍገመገማል፤ ከዚያ ወይ ይወድቃል፤ ወይ ሚዛኑን አስተካክሎና ተስተካክሎ ይቆምና ይቀጥላል።

በመንፈሳዊ ጉዞ ውስጥ ብዙ መሰናክሎችና አሳናካዮች አሉ። የጠላት ኃይል ባየለበት የውጊያ ወረዳ ውስጥ እንዳለ ሰው እንመስላለን። ሰይጣን በሚጋልብባት ዓለም ውስጥ አለን። ስሕተቶችና አሳቾች በበዙበት እንመላለሳለን። በወደቀና ለኃጢአት በቀላሉ በሚሸነፍ አዳማዊ ሥጋ ውስጥ እንገኛለን። በዚህ ውስጥ ግን በውስጣች ሆኖ ብርታትን በሚሰጠን፥ ከውጪ ከሚመጣ ማናቸውም ጥቃትም ሊጠብቀን፥ ቅዱሳንን ከመሰናከል፥ ከመጠለፍ፥ ከመውደቅ ሊጠብቅ በሚቻለው በእግዚአብሔር እጅ ተጠብቀናል። ይህ ድንቅ ዋስትና ነው። እርሱ በዚህ ጉዞ ውስጥ ቅዱሳኑን ይጠብቃል። ለመውደቅ እንዳይሰናከሉ ይጠብቃል።

በዚህ ጉዞ ውስጥ ብቻ አይደለም። ይህ ጉዞ አንድ ቀን ያበቃል፤ ያከትማል። አንድ ቀን በፊቱ እንቆማለን። በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ፤ ቅዱሳኑ በፊቱ የሚቆሙት ናቸው። ግን የሚያቆማቸው አለ፤ ያንን ነው ይሁዳ የሚለው። እኛ በፊቱ የምንቆመው ነን፤ የሚያቆመንም እርሱ ራሱ ነው። በቀላል ምሳሌ ብናየው፥ አንድን ትንሽ ልጅ ስናጫውት ወይ ስናሯሩጥ፥ ወይ ስናሠራ ቆይተን፥ በመጨረሻው በገንዳ ውስጥ አጥበን፥ አጽድተን፥ አንጽተን በፎጣ ጅቡን አድርገን አውጥተን እፊታችን አቁመን፥ ትከ ብለን አይተን ግንባሩን ብንስመው ሁሉን ያደረግን እኛ ነን። የቆመው እርሱ ነው፤ ያቆምነው እኛ ነን። በመንፈሳዊ ጉዞአችን ከመፈጠራችን እስከ መዳናችን፥ እስከ ማገልገላችንና በፊቱ እስከመቆማችን ድረስ አድራጊውና ተመስጋኙ እኛ ሳንሆን እርሱ ነው። እኛ ያደረግነው ነገር ቢኖር ያንን ያደረግነው እርሱ በሰጠን ጸጋና ጉልበት ብቻ ነው። የፈጠረን፥ በቅዱስ አጠራር የጠራን፥ ያዳነን፥ ያጸደቀን፥ ጸጋን ያደለን፥ በእጁ የያዘን፥ በቀኑ ፍጻሜም በፊቱ የሚያቆመን እርሱ ነው።

በተለይ ከስሕተት ትምህርትና ከሐሰት አስተማሪዎች ለመጠንቀቅ ተብሎ በተጻፈ መልእክት ውስጥ እንዲህ ያለ ተስፋና ዋስትና መስፈሩ የአማኞች ልብ እንዳይርድ የሚደግፍ እውነት ነው። እንዲያውም በተቃራኒው ደስታና ሐሴት ያለበት ነው። በፊቱ ነውር የሌለን ሆነን የምንቆመው በደስታ ነው። ይህ ደስታ የደስታዎች ሁሉ ቁንጮ ነው።

ይህ ቅዱሳንን ነውር የሌለባቸው አድርጎ የማድረጉ እውነት በሐዋርያው ጳውሎስም የተጻፈ ትምህርት ነው፤ ኤፌ. 1፥4፤ 5፥27፤ ቆላ. 1፥22። የቅዱሳን ነው የለሽ ሆኖ የመቆም ምንጩና መነሻው ደግሞ ጴጥሮስ ያብራራው ነውርና እድፍ በሌለው የክርስቶስ ደም የተዋጀን መሆናችን ነው፤ 1ጴጥ. 1፥19።

የፍጻሜው ውበት ደግሞ በፍጻሜው የቅዱሳን በክብሩ ፊት መቆማችን ነው። የምንቆመው ደግሞ በእርሱ ፊት ነው፤ በክብሩ ፊት፤ ክቡር በሆነው በእርሱ። ፍጻሜያችን ይህ መሆኑ እንዴት ድንቅ ነው! በፈጠረን በሥራን፥ በዋጋ በገዛን፥ በጠበቀን፥ ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንድንሆን በወደደው አምላክ በእግዚአብሔር ፊት የመቆማችን ቀን እንዴት ድንቅ ቀን ነው! ይሁዳ ይህን አምላክ ከገለጠው በኋላ በቁ 25 ይህን ላደረገውና ለሚያደርገው ለዚህ አምላክ የተገባውን አክብሮት ጽፎ ደመደመ።

ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን። እርሱ ብቻውን የሆነ አምላክ ነው። ሌላ ማንም አምላክ ከእርሱ በቀር የለም። አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ ሰዎች አመለኳቸው እንጂ አምላክነት የላቸውም። እርሱ ግን ብቻውን አምላክ ነው። ይህ አምላክ መድኃኒትም ወይም አዳኝም ነው። ፈጣሪና ገዢ፥ ወይም ባለቤትና ጌታ ብቻ ሳይሆን ከውድቀትና ከጥፋት፥ ከሞትና ከኩነኔ የሚታደግ አዳኝም ነው። ይህ ርቀትና ረቂቅነትን ብቻ ሳይሆን ቅርብነቱንና ወዳጅነቱን የሚያሳይ እውነት ነው።

ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን። እርሱ ክብር የተገባው ጌታም ነው። ለክብሩ የጊዜ ወሰን የለውም። ጊዜ ወይም ዘመን የተፈጠረ ነገር ነው። ከዘመን መፈጠር በፊት እግዚአብሔር በክብሩ ተከብሮ ነበረ። በግርማው ነበረ። ግርማ የባለ ሥልጣን ታላቅነት ነው። በኃይልም ነበረ። ይህ ኃይል የተሰኘው ግዛትንና ገዢነትን የሚያሳይ ቃል ነው። በሥልጣንም ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ የተፈጠረ ነውና በቁጥጥሩ ሥር የሆነለት አምላክ መሆኑን ያሳያል። እነዚህ ሁሉ ከዘመን በፊት የሆኑ ነገሮች ብቻ አይደሉም። አሁንና እዚህም እግዚአብሔር በእነዚህ የማንነቱ መግለጫዎች ተገልጦ

አለ። አሁንም ክቡር፥ አሁን፣ ባለ ግርማ፥ አሁንም ኃያል ወይም ገዢ፥ አሁንም ባለ ሥልጣን ነው። ይህ የሚያሳርፍ እውነት ነው። ይህ ደግሞ ያለፈና የአሁን ብቻ ሳይሆን እስከ ዘላለም ድረስም እውነት ሆኖ የሚኖር ነው።

ይህ ሁሉ ለእርሱ የሚሆነው ደግሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። የድነታችን መስመሩ፥ የእምነታችን ራስና ፈጻሚው፥ ወደ አብ የመሄጃው መንገድ፥ የመግቢያው በር እርሱ ነው። ጸሎታችን በስሙ፥ ምስጋናችንም በእርሱ በኩል ነው። የእርሱ ባሪያ መሆኑን በመግለጥ ጀምሮ ክብርን በእርሱ በኩል አስተላልፎ ደመደመ።

ይሁዳ በመግቢያው ቃል ለቅዱሳን ምሕረት ሰላምና ፍቅር እንዲበዛላቸው የጻፈውንና እዚህ ደግሞ ባለመሰናከል ስለመጥጠበቅና በክብሩ ፊት ስለመቆም የጻፈውን በመዝጊያው ጥቅስ ስለ እግዚአብሔር ከጻፈው ጋር አስተያይተን ስናጤን ትልቅ እውነት እንጨብጣለን። ለቅዱሳን የሚያስፈልገን በጎነቱ እና ለእግዚአብሔር የተገባው ክብሩ በደማቅ ቃላት ተገልጠዋል።

እኛንም ሳንሰናከል እንዲጠብቀን፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌለን አድርጎ እንዲያቆመን ለሚችለው፥ ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን።